# بسم الله الرحمن الرحيم

በአላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ በጣም ርህሩህ ለሆነው ምስጋና ለአለማቱ ጌታ አላህ ይሁን ሰላትና ሰላም በነብዩ መሀመድ እና በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረባቸው ላይ ይሁን።

## መግቢያ

በቃላት አገባብ እንደሚታየው ሽብርተኝነት በማህበረሰቡ ዘንድ ሊጠነቀቁትና በየትኛውም መንገድ እናሁኔታ ሊዋጉት የሚገባ መትፎ ወይም አጠያፊ ነው ።ይህ የቃል አገባብ ግን ከ14ኛው ክፍለ ዘመን በፊት እስልምና የደረሰበት (የሰጠው)ትርጉም መድረስ አልቻለም። በትርጉሙ መሰረት ሽብርተኝነት በእስልምና በሁለት ይከፈላል። መልካም ሽብርተኝነት እና አጸያፊ ሽብረተኝነት ይባላል።

አጸያፊ ሽብርተኝነት የሚባለው፡-ጠቅለል ባለ መልኩ ያለ ምንም በቂ ምክንያት በሌሎች ላይ በደል እና ጥቃት ማደረስ ነው።

ይህ አገላለጽ የተሰጠው ከዚህ ሁሉ ንጹህ የሆነው የእስልምና ሐይማኖት እና ሙስሊሙ ማህበረሰብ የእስልም ሐይማኖት እውቀት የሌላቸው ብዙዎቹ ዘንድ የዘውትር መገለጫው አድርገውታል ይህ ደሞ ሆን ተብሎ በተወሰኑ ሰዎች (ቡድኖች) በዙርያቸው ለሚደረገው እና በተቃራኒው ስለሚወራባቸው ነገር ትኩረታቸውን (እይታቸውን)ለመስረቅ ነው። ሆን ተብሎ ስለመደረጉ ማስረጃ የሚሆነው ደግሞ እስልምና ሐይማኖት እና ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በሽብርተንነት መፈረጅ ነው። ይህ ደግሞ ሰዎችን ከዚህ ታላቅ ሐይማኖት ለማባረር ታልሞ እና ታቅዶ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው።

እስልምና እና ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)በሽብርተኝነት የገለጹት ለነዚያ በገፍ ኑጹሃንን የጨረሱ እለት ተእለት የፍልስጤም ኑጹሃን ሴቶች እና ህጻናት በሽብር የገደሉ ይህ ስም አልሰጣቸውም፡ ፡ እነዚያ በሐይል ሐገርን የተቆጣጠሩ ህዝቦችን ከቀያቸው ያፈናቀሉ ምን ያህል ነው። ቬትናም ላይ የተገደለው ምን ያህል ነው በኑክሌር ቦምብ በጃፓን ላይ የተገደለው ምን ያህል ነው። ቦስንያ እና ሄርዞሳቫንያ የተገደለው ምን ያህልስ ነው። ፍልስ ጤም ውስጥ በየቀኑ የሚገደለው ? ስንት እና ስንት ናቸው? ሙስሊም ያልሆኑ ለግድያ ለመፈናቀል እና ለውድመት ሰበብ ሆነው ሳለ ይስም ያልተሰጣቸው ይባስ በለው ነፍስ አዳኝ እና ነጻ አውጪ የሚል ስም የተሰጣቸው ።

መልካም ሽብርተንነት የሚባለው ቁዱስ ቁርዐን ሙስሊሞችን ባዘዘው መሰረት ጠላት እንዳያጠቃቸው እና ለማጥቃት እንዳያስቡ የመከላከያ ሀይል እንዲያደራጁ ነው። አላህ እንዲህ ይላል (ይህ የሽብርተኝነት እሳቤ ሁሉ ሐገሮች ጦራቸውን ለማደራጀት እና ለማዳበር አዲስ በሆነ አገር ለማሳደግ ጠላቶቻቸውን ለማስፈራራት ይተገብሩታል ። በዚህ ሁኔታ አጸያፊ ሽብርተኝነት እና የህዝብ ጥቅም ወራሪዎቻችን ለመከላከል የማደራጃ ህጋዊ መከላከያ ሊለይ ይገባል። አላህ እንዲህ ይላል(አል በቀራዕ 190)

وَقَاتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ الَّذِينَ يُقَاتِلُونَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوا ۚ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْمُعْتَدِينَ [٢:١٩٠]

‹‹እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፡፡ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎን አይወድምና፡፡››

አጸያፊ ሽብርተኝነት ያለምንም ምክንያት እና አነቃቂ ነገሮች ሳይኖሩ አይፈጠርም ። ሽብርተኝነት እንደሚታወቀው በክፍተት አይነሳም የሚነሳው ጫና በዝቶ ለመቋቋም የሚቸግር ጭቆና ሲኖር ነው።

(የጫና መብዛት ፍንዳታን ትወዳለች) እንደሚባለው ትክክለኛው ሽብርተኝነት ማለት አጸያፊ ሽብርተኝነት ነው። ይህም ሰዎችን በመበደል ሀገራችንን በመዐዘር ገንዘባቸውን መበዝበዝ ንብረታቸውን መንጠቅ

ነጻነታቸውን መጋፋት ለራስ አላማና ግብ ለማሳካት በሰው ጉልበት መጠቀም ነው፡፡ ይህ ደግሞ በብዙ አገራት የምናየው ዘዴዎችና ስርአቶች በውጪ ቢያስመስሉም አላማቸው ግን የሰው ልጅ ደስታ መጠበቅ ሳይሆን የተወሰኑ ቡድኖችን መስእዋት አድርጎ የተወሰነ ቡድን ደስታ መጠበቅ የአንድ ሐገር ደስታ መስእዋት አድርገው የአንድ ሀገር ደስታ (ፍላጎት) መጠበቅ ነው፡፡ ስርአቱ አላህ የፈጠረው የሰው ዘር በሙሉ የጋራ ጥቅም ለማሳካት ሳይሆን እንዳል ነው የተወሰኑ ሀገራት ወይም ዘር ፤ ቀለም ፤ጊዜ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህም የስርአቱ መበደል እና ሰው ማጣት ውጤት ነው፡፡

የእስልምና አጠቃላይነት እና አለም አቀፋዊነት ስን መለከት ዘርን ከዘር ቡድንን ከቡድን አለያየም፡፡

ከተቃራኒ ወገን እና ከጠላት ጋር ሲከተለው የነበረው ግኑኝነት እና ስርአት ጥላቻቸውን ለማስወገድ ትልቅ ሚና ነበረው፡፡ ይህም ከማስመሰል ከውሸት እዩልኝ ከማለት የራቀና ወደ እውነት የምትጠራውን ስርአት ፍትህ እና በደልን በማስወገድ ግልጽየሆነ ግኑኝነት በመፍጠሩ ነው በርካታ ጠላቶች ከጠቅላላው ይሁንከሙህራን ወደ ጎራ በማምጣት ውታማ ሆነዋል፡፡ በተለይ ደሞ እነዚያ አስተሳሰባቸው ካለመቻቻል የላቀ እና ፍትሐዊ የሆነ አስተሳሰብ ያላቸው፡፡

የእስልምና ስርአት አላማው ባጠቃላይ ለሰው ዘር በሙሉ ለህብረተሰቡ ማገልገል ይህም ከሌላውጋር ማገልገል ይህም ከሌላው ጋር በፍቅር ፤ በሰላም ፤ በመዋደደ የሚኖር ማህበረሰብ ለመፍተር ይጠቅማል፡ ፡ አላህ እንዲህ ይላል ፡-

إِنَّمَا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ قَاتَلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَأَخْرَجُوكُم مِّن دِيَارِكُمْ وَظَاهَرُوا عَلَىٰ
إِخْرَاجِكُمْ أَن تَوَلَّوْهُمْ ۚ وَمَن يَتَوَلَّهُمْ فَأُولَٰئِكَ هُمُ الظَّالِمُونَ [٦٠:٩]

‹‹አላህ የሚከለክላችሁ ከእነዚያ በሃይማኖት ከተጋደሉዋችሁ፣ ከቤቶቻችሁም ካወጡዋችሁ፣ እናንተም በማውጣት ላይ ከረዱት (ከሓዲዎች) እንዳትወዳጁዋቸው ብቻ ነው፡፡ ወዳጅ የሚያደርጓቸውም ሰዎች እነዚያ እነርሱ በዳዮቹ ናቸው፡፡››

ይህ አጠር ያለ መግቢያ ለነዚያ እውነትን ለሚፈልጉ ካለመቻቻል ስሜት የጸዱ የእስልምና ስርዐት፤ አስተምህሮ እና መመርያ ማወቅ ለሚፊፈልጉ ማበረታቻ እንዲሆናቸው እመኛለሁ፡፡ የዚህ ታላቅ ሐይ ማኖት ውበት እና ጥቅም ግልጽ እንዲሆንላቸው በእርግት ይህ ስሜት በትክክል ምድር ላይ በሐይማኖቱ የኖረና የሞከረው ብቻ ነው ሚረዳው፡፡

እስልምና ከጀመረበት አንስቶ አሁን እስካለንበት ጊዜድረስ ያለው ትልቅ ጽናት ማስረጃ ይሆነናል፡ ፡ ከሙስሊሙ በኩል የሚገኘው የሰው እና ቁሳዊ ድጋፍ አናሳ በሆነበት እና በምላሹ የሐይማኖቱ ተቃዋሚዎች እና ጠላቶች በቁሳዊ እና በሰው ሀይል ለማዳከም እና ሰዎች ሐይማኖቱን እንዲ ጠሉት በማድረግ ቢሰሩም ይህ ሁሉ እየሆነ ግን ሰዎች ወደ ሐይማኖቱ ቡድን ይገባሉ ለምን?

ምክንያቱም ግልጽ እና የተፈጥሮ ሐይማኖት እና አዕምሮ የሚቀበለው ሐይማኖት ስለሆነ ነው፡፡ የሰው ልጅ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ሁሉንም ፍላጎት ሚዛናዊ በሆነ ስርአት የሚያሟላ ሐይማኖት ነው፡፡

የሰው ልጅ ከሽብር ጥቀቶች የሚከላከል እና የስን ልጅን ቁሳዊ በሆነ ነገር የእንስሳ ነት ባህሪ ተላብሰው ስሜቶቻቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን ከማርካት የላቀ ሐይማኖት ነው፡፡

በዚህ አጠር ባለ መግቢያ ለማስታወስ የፈለኩት ይህን ነው  ይህቺ ትንሽ ስራ ጠቃሚ እና ለአላህ ተብሎ የተሰራ ስራ እንዲሆን አላህን እለምናሁ፡፡ የሚጠቅም እና የተጻፈለት አላማ እና ግብ የማያሳካ እንዲሆን አላህን እጠይቃለሁ፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መልካም የሆነው ከአላህ (ሱ.ወ) ሲሆን ስህተት እና ጎዶሎው ደግሞ ከኔና ከሸይጣን ነው፡፡ ለዚህም አላህን(ሱ.ወ) ምህረት እጠይቃለሁ ፡፡  ሰላት እና

ሰላም በረከት በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና በቤተሰቦቻቸው ላይ በባልደረቦቻቸው ላይ እንዲሁም በሳቸው የተመራ እስከመጨረሻው ቀን መንገዳቸውን የተከተለ ላይ ይሁን ።

# <u>የእስልምና ትርጉም</u>

ለአንባቢውግልፅእንዲሆን፡ሰላምየሚለውቃልበእስልምናስፍያለትርጉምይይዛል፡፡
ከሰውልጅአገዛዝነፃመሆንናየመረጋጋትመንፈስይኖረዋል፡፡

እስልምናማለት፡ለአላህ
(ሱ.ወ)እጅመስጠትእናበነፍስምበስጋምመተናነስሲሆንይህምያለተቃውሞመታዘዝየከለከለውንበመከልከልበው
ሳኔውአምኖለህግናስርዓቱማደርነው፡፡አለህ (ሱ.ወ) ለነብዩኢብራሂም (ዓ.ሰ)ሲያናግራቸው፡-

إِذْ قَالَ لَهُ رَبُّهُ أَسْلِمْ ۖ قَالَ أَسْلَمْتُ لِرَبِّ الْعَالَمِينَ [٢:١٣١]

ጌታው ለርሱ ታዘዝ ባለው ጊዜ (መረጠው)፡፡ ለዓለማት ጌታ ታዘዝኩ አለ፡፡

(አልበቀራ131)

ይህነውትክክለኛእስልምናሁሉምሰውሊላበሰውየሚገባው ፡አላህ (ሱ.ወ)እንዲህይላል፡-

قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ [٦:١٦٢]

«ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል፡፡ (አል አንዓም 162)

ሰላም ፡ችሎታውየላቀውየፅዱስምባለቤትየሆነውጌታየአላህ(ሱ.ወ)ከሰሞችውስጥአንዱነው፡፡
አላህእንዲህይላል፡-

هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ ۚ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ [٥٩:٢٣]

‹‹እርሱ አላህ ነው፡፡ ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ፣ ጸጥታን ሰጪው፣ ባሮቹን ጠባቂው፣ አሸናፊው፣ ኀያሉ፣ ኩሩው ነው፡፡ አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ፡፡›› (አልሐሸር 23)

ሰላም ፡ከጀነትሰሞችውስጥአንዱነው፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

لَهُمْ دَارُ السَّلَامِ عِندَ رَبِّهِمْ ۖ وَهُوَ وَلِيُّهُم بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ [٦:١٢٧]

ለእነርሱ በጌታቸው ዘንድ የሰላም አገር አላቸው፡፡ እርሱም (ጌታህ) ይሠሩት በነበሩት ምክንያት ረዳታቸው ነው፡፡(አልአንዓም127)

ሰላምየጀነትሰዎችሰላምታየሚለዋወጡበትቃልነው፡አላህከነሱያርገንአላህእንዲህይላል፡-

تَحِيَّتُهُمْ يَوْمَ يَلْقَوْنَهُ سَلَامٌ ۚ وَأَعَدَّ لَهُمْ أَجْرًا كَرِيمًا [٣٣:٤٤]

በሚገናኙት ቀን መከባበሪያቸው ሰላም መባባል ነው፡፡ ለእነርሱም የከበረን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል፡
፡ (አልአሕዛብ44)

ሰላምሙስሊሞችእርስበርሳቸውሰላምታየሚላዋወጡበትቃልናት(ሰላም የአላህ እዝነት እና በረከት በናንተ ላይ ይሁን )ምነኛ ያማረች ሰላምታ ጣፍጭ ንግግር ናት የሰሚው ቀልብ የምታቀርበ ጥላቻና መራራቅን የምታባርር ለነፍስም መረጋጋትና እረፍትን የምታስፍን ናት፡፡ሰላምታ አማን እና ኢማን የሚለውም ትርጉም ይይዛል፡ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ የኢማን ማሟያ እንደሆች የተናገሩት ሀዲስ እንደሚከተለው ይሆናል(እስካላመናቹ ጀነት አትገቡም እሰካልተዋደደቹ አታምኑም ከሰራቹት የምትዋደዱበትን ነገር ልጠቁማቹ እርስ በርሳቹ መሀከል ሰላምታ አብዙ)(ሙስሊም)

ነብዩ ሰ.ዐ.ወ መልካም ስራ ናት ብለው ይገልፆታል (የትኛው ስራ ነው መልካም ስራ ? ተብለው በተጠየቁ ጊዜ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ አሉየተራበን ማብለት ፣ለወቅከውምላለወቅከውም ሰላምታ መሰጠት (ቡኻሪ እና ሙስሊም)

ወደ እስልምና መግባት የተፈለገበት ዋናው ኣላማ የአላህን ሱ.ወ ፍላጎት መከተል በመመርያው መሰረት ህይወትን መምራት፡ ወደ ኸይ ር የሚመራንን መንገድ በመከተል ይሆናል፡፡ አላህእንዲህ ይላል፡-

يَا أَهْلَ الْكِتَابِ قَدْ جَاءَكُمْ رَسُولُنَا يُبَيِّنُ لَكُمْ كَثِيرًا مِّمَّا كُنتُمْ تُخْفُونَ مِنَ الْكِتَابِ وَيَعْفُو عَن كَثِيرٍ ۚ قَدْ جَاءَكُم مِّنَ اللَّهِ نُورٌ وَكِتَابٌ مُّبِينٌ يَهْدِي بِهِ اللَّهُ مَنِ اتَّبَعَ رِضْوَانَهُ سُبُلَ السَّلَامِ وَيُخْرِجُهُم مِّنَ الظُّلُمَاتِ إِلَى النُّورِ بِإِذْنِهِ وَيَهْدِيهِمْ إِلَىٰ صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ

የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ ከብዙውም የሚተው ሲኾን መልክተኛችን (ሙሐመድ) በእርግጥ መጣላችሁ፡፡ ከአላህ ዘንድ ብርሃንና ገላጭ መጽሐፍ በእርግጥ መጣላችሁ፡፡አላህ ውዴታውን የተከተሉትን ሰዎች የሰላምን መንገዶች በእርሱ ይመራቸዋል፡፡ በፈቃዱም ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል፡፡ ወደ ቀጥተኛም መንገድ ይመራቸዋል፡፡(አልማኢዳህ 15-16)

እስልምና ሀይማኖት ሰላምአጠቃልላየያዘችውን ትርጉም ሁሉ የያዘ ሀይማኖት ነው፡፡ ነብዪ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ ብለዋል (ሙስሊም ማለት ምላሱም እጅም ሙስሊሞችን ከመንካት የጠበቀ ነው ፡ስደተኛ ማለት ደግሞ አለህ ወደ ከለከለው ነገር የተሰደተ ነው)በሌላ ሀዲሳቸው ( ሙእሚንማለት ሰው ያመነው ነው) (ቡኻሪ እና ሙሰሊም)

በአለም አቀፍ ደረጃ በሙስሊሙ ማህበረሰብእና ከሙሰሊሙ ውጭ ባለው ማሕበረሰብ በእምነትና በመረጋጋት ከጥቃት ነፃ የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር በተለይ ደግሞ በሀይማኖት ድርድር ለማያቁት ማህበረሰብ ወሳኝ ነው፡፡ አለህ እንዲህይላል፡-

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ሁላችሁም በመታዘዝ ውስጥ ግቡ፡፡ የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከተሉ፤ እርሱ ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነውና፡፡ (አልበቐራህ 208)

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا ادْخُلُوا فِي السِّلْمِ كَافَّةً وَلَا تَتَّبِعُوا خُطُوَاتِ الشَّيْطَانِ ۚ إِنَّهُ لَكُمْ عَدُوٌّ مُّبِينٌ [٢:٢٠٨]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ሁላችሁም በመታዘዝ ውስጥ ግቡ፡፡ የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከተሉ፤ እርሱ ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነውና፡፡»

## እሰልምና የተስፋፋው በማሰገደድ ነው ?

**በጠላት ምላስተደጋግመው የሚነገሩት እንደዚህ አይነትስህተቶች መሠረታዊ የእስልምና ትምህርት እርማት ይሰጣል፡፡ አላህእንዲህ ይላል ፡-**

لَا إِكْرَاهَ فِي الدِّينِ ۖ قَد تَّبَيَّنَ الرُّشْدُ مِنَ الْغَيِّ ۚ فَمَن يَكْفُرْ بِالطَّاغُوتِ وَيُؤْمِن بِاللَّهِ فَقَدِ اسْتَمْسَكَ بِالْعُرْوَةِ الْوُثْقَىٰ لَا انفِصَامَ لَهَا ۗ وَاللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ [٢:٢٥٦]

«በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡ በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፡፡ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡»

(**አልበቐራህ** 256)

أَفَأَنتَ تُكْرِهُ النَّاسَ حَتَّىٰ يَكُونُوا مُؤْمِنِينَ [١٠:٩٩]

‹‹ ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲኾኑ ታስገድዳለህን=››**በሌላ ምዕራፍ** (**ዩኑስ** 99)

وَقُلِ الْحَقُّ مِن رَّبِّكُمْ ۖ فَمَن شَاءَ فَلْيُؤْمِن وَمَن شَاءَ فَلْيَكْفُرْ ۚ

‹‹ «እውነቱም ከጌታችሁ ነው፡፡ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ» በላቸው፡፡»

فَإِن تَوَلَّوْا فَإِنَّمَا عَلَيْكَ الْبَلَاغُ الْمُبِينُ [١٦:٨٢]

‹‹ (ከኢስላም) ቢሸሹም ባንተ ላይ ያለብህ ግልጽ ማድረስ ብቻ ነው፡፡››**በሌላምዕራፍ**(**አል ነሕል**82)

فَذَكِّرْ إِنَّمَا أَنتَ مُذَكِّرٌ [٨٨:٢١]

‹‹ አስታውስም፤ አንተ አስታዋሽ ብቻ ነህና፡፡››

لَّسْتَ عَلَيْهِم بِمُصَيْطِرٍ [٨٨:٢٢]

«በእነርሱ ላይ ተሿሚ (አስገዳጅ) አይደለህም፡፡»በሌላ ምዕራፍ (አል ቓሽያ22)

**እስልምናአስገዳጅ ሀይማኖት አለመሆኑንየሚጠቅሱብዙ ምዕራፎች አሉ፡፡ እስልምናሀይማኖት እምነት ነው ፡ እንደመሆኑም እምነቱ በልብ ውስጥ መፅናት እንዳለበት እና በምላስ መናገር ብቻ በቂ አለመሆኑ ኣላህ በቁርአኑ እንዲህ ሲል ያሰረዳናል፡፡**

قَالَتِ الْأَعْرَابُ آمَنَّا ۖ قُل لَّمْ تُؤْمِنُوا وَلَٰكِن قُولُوا أَسْلَمْنَا وَلَمَّا يَدْخُلِ الْإِيمَانُ فِي قُلُوبِكُمْ ۖ وَإِن تُطِيعُوا اللَّهَ وَرَسُولَهُ لَا يَلِتْكُم مِّنْ أَعْمَالِكُمْ شَيْئًا ۚ إِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ [٤٩:١٤]

«የዐረብ ዘላኖች «አምነናል» አሉ፡፡ «አላመናችሁም፤ ግን ሰልመናል በሉ፡፡ «እምነቱም በልቦቻችሁ ውስጥ ገና (ጠልቆ) አልገባም፡፡ አላህንና መልክተኛውንም ብትታዘዙ ከሥራዎቻችሁ ምንንም አያጎድልባችሁም፡፡ አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና» በላቸው፡፡» (አል ሑጁራት14)

**ልብ ውስጥ የፀና በሀይልና በጉልበት ማውጣትአይቻልም: የሰውልጅልቡ (ውስጡ)ያለመነበትነገር በምለሱ ሊናገር ይችላል ይህንን ደግሞ እስልምናአይደግፈውም፡፡ኣላህ እንዲህ ይላል**

مَن كَفَرَ بِاللَّهِ مِن بَعْدِ إِيمَانِهِ إِلَّا مَنْ أُكْرِهَ وَقَلْبُهُ مُطْمَئِنٌّ بِالْإِيمَانِ وَلَٰكِن مَّن شَرَحَ بِالْكُفْرِ صَدْرًا فَعَلَيْهِمْ غَضَبٌ مِّنَ اللَّهِ وَلَهُمْ عَذَابٌ عَظِيمٌ [١٦:١٠٦]

ከእምነቱ በኋላ በአላህ የካደ ሰው (ብርቱ ቅጣት አለለው)፡፡ ልቡ በእምነት የረጋ ኾኖ (በክህደት ቃል በመናገር) የተገደደ ሰው ብቻ ሲቀር፡፡ ግን ልባቸውን በክሕደት የከፈቱ ሰዎች በነሱ ላይ ከአላህ ቁጣ አለባቸው፡፡ ለእነሱም ታላቅ ቅጣት አልላቸው፡፡ (አልነሕል 106)

## እስልምና በሀይል የተስፋፋ ሀይማኖት ነውን ?

ለሁሉም ስርዓት የሚጠብቀው፡ ሰርአቱን የሚያከብር እና ከሰርአቱ የሚያፈነግጠውን የሚቀጣ ሀይል ያስፈልገዋል፡፡ይህ ሀይል ደግሞ ስርኣቱን ለማስፈፀም እና ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡ ፡ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ ብለዋል፡- "በቁርአን ትዕዛዝ ያልተገራ ሰው በሀይል እና በሰልጣን ይገራል" ፡፡

በመጀመርያዎቹ የእስልምና ጥሪ ወቅት አጠር ያለች ታሪክ እንውስድ ፡ ነብዩ ሰ. ዐ.ወ የመካ ህዝብ ወደ እስልምና በመልካ|ም ንግግር ሲጠሩ 13 ዓመታትን ቆይተዋል ፡ በዚ ዓመታት ግን ከህዝቡ ያገኙት ምላሽ ማስተባበያ፣ግፍ እና እንግልት ነበር ፡፡ ይባስ ብለው በአማኞችላይ ስቃይ እና መከራ ማድረስ ጀመሩ ፡ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ አማኞች ሲቀጡባዩ ጊዜ ትእግስት እንዲያደርጉ ከመናገር ውጭ ሌላ ኣማራጭ አልነበራቸውም ፡፡ ዓማር እና እናቱ ሱመያ ሲያሰቃይዋቸው ባዩ ጊዜ (እናንተ የያሲር ቤተሰቦች ትእግስት አርጉ በእርግጥ ጀነት አለላቹ) ብ ለው ነበር ያለፉት ፡፡ ቅጣቱ እስከ ሞት ደረጃ ደርሶ እንኳን ነብዩ ሰ.ዐ.ወ(ጌታየ ሆይ ህዝቦቼን ማርልኝ ባለማወቃቸው ምክንያት ነው)ብለውዱዓ ከማድረግ አልቦዘኑም፡፡

አላህሱ.ወ በተለያዩ ምዕራፍ ለነብዩ ሰ.ዐ.ወ ትእግስትእንዲያደርጉ እና ከ እሳቸው ውጭ በነበሩት ነብያቶችምችግር እና መከራ እንደደረሰባቸውገልፆ ለህቅየሚደርግ ጥሪ ረዥም እና ከባድ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ምክንያቱም በእውነት እና በውሸት በጥሩእና በ መጥፎ የሚደረግ ጦርነት እንደሆነ በቁርኣኑ ገልፆታል ፡፡አላህእንዲህይላል

فَاصْبِرْ كَمَا صَبَرَ أُولُو الْعَزْمِ مِنَ الرُّسُلِ وَلَا تَسْتَعْجِل لَّهُمْ ۚ

‹‹ ከመልክተኞችም የቆራጥነት ባለቤቶች የኾኑት እንደ ታገሱ ሁሉ ታገስ፡፡ ለእነርሱም (ለሕዝቦችህ ቅጣት) አትቻኮል፡፡››(አልአህቃፍ 35)

ነብዩ ሰ.ዐ.ወ በየ አመቱ ወደ መካ ለሀጅ የሚመጡትን የተለያዩ የአረብ ጎሳዎች ጥሪ ማደረግ ቀጠሉ ከመዲና የመጡ ሰዎችም ለጥሪው ምላሽ ሰጡ፡፡ለነብዩሰ.ዐ.ወ ወደ ሀገራቸው ከመጡ ረዳት እንደሚሆንዋቸው እና ከጥቃት እንደሚጠብቅዋቸው ቃልገብተው ተመለሱ፡፡ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እና ሀይማኖቱን የተቀበሉ አማኞች ወደ መዲና ተሰደቱ፡፡አስራ ሶስተ ዓመት መካ በቆዩበት ጊዜ ግን አንድ ጠብታ ደም አላፈሰሱም፡፡ቁረይሾች በእሳቸውም ሆነ በተከታዮቻቸው ንብረትና ገንዘብ ይህ ተብሎ የማይገለፅ የመብት ጥስት አድርሰውባቸው እንኳን ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ጦርነት አላወጁም፡፡መዲና በገቡ ከሁለት ዓመት ቡሃላ የተካሄደው የበድር ጦርነት ነበር፡፡ይህም ጦርነት ሙስሊሞች አልጀመሩትም፡፡በወቅቱ ጠላትን ወይም ንብረትን መማረክ እንዲሁም ድንበር ጥሰቱን እንዲገታ ምላሽ መሰጠቱ ግድነበር፡፡በመሆኑም መካ በነበሩበት ጊዜ በቁረይሾች የተዘረፉትን፣የተቀሙትን

ጥለው እንደሰደዱ የተገደዱትን ንብረት እና ገንዘባቸው ለማሰመለስ ከመዲናወጡ፡፡ከሻም ወደ መካ ሲ.ጋዝ የነበረ የንግድ ቅፍለት እስልምና ከመቀበሉ በፊት በቁረይሾች አለቃ አቡሱፍያን ይመራ ነበር ፡ሆኖም መስሊሞች ሳያገኙት የቅፍለቱን መስመር ቀይሮ አመለጠ፡፡መረጃው የደረሳቸው ቁረይሾች አሰፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ነብዩሰ.ዐ.ወ ለመዋጋት መጡ፡፡በእስልምና ታሪክ የመጀመርያው ጦርነት ሆኖ ተመዝግበዋል፡፡ ድሉም ለነቢዩ ሰ.ዐ.ወ እና ለተከታዮቻቸው በመሆን ተፈፅመዋል ፡፡ አለህም በቁርአኑ እንዲህሲልይገልፀዎል

أُذِنَ لِلَّذِينَ يُقَاتَلُونَ بِأَنَّهُمْ ظُلِمُوا ۚ وَإِنَّ اللَّهَ عَلَىٰ نَصْرِهِمْ لَقَدِيرٌ [٢٢:٣٩]

«ለእነዚያ ለሚገደሉት (ምእመናን) እነርሱ የተበደሉ በመኾናቸው (መጋደል) ተፈቀደላቸው፡፡ አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥ ቻይ ነው፡፡»

الَّذِينَ أُخْرِجُوا مِن دِيَارِهِم بِغَيْرِ حَقٍّ إِلَّا أَن يَقُولُوا رَبُّنَا اللَّهُ ۗ وَلَوْلَا دَفْعُ اللَّهِ النَّاسَ بَعْضَهُم بِبَعْضٍ لَّهُدِّمَتْ صَوَامِعُ وَبِيَعٌ وَصَلَوَاتٌ وَمَسَاجِدُ يُذْكَرُ فِيهَا اسْمُ اللَّهِ كَثِيرًا ۗ وَلَيَنصُرَنَّ اللَّهُ مَن يَنصُرُهُ ۗ إِنَّ اللَّهَ لَقَوِيٌّ عَزِيزٌ [٢٢:٤٠]

«ለእነዚያ «ጌታችን አላህ ነው» ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከአገራቸው የተባረሩ ለሆኑት (ተፈቀደ)፡፡ አላህ ሰዎችን ከፊላቸውን በከፊሉ መገፍተሩ ባልነበረ ኖሮ ገዳማት፣ ቤተክርስቲያኖችም፣ ምኩራቦችም በውስጣቸው የአላህ ስም በብዛት የሚወሳባቸው መስጊዶችም፤ በተፈረሱ ነበር፡፡ አላህም ሃይማኖቱን የሚረዳውን ሰው በእርግጥ ይረዳዋል፡፡ አላህ ብርቱ አሸናፊ ነውና፡፡»

الَّذِينَ إِن مَّكَّنَّاهُمْ فِي الْأَرْضِ أَقَامُوا الصَّلَاةَ وَآتَوُا الزَّكَاةَ وَأَمَرُوا بِالْمَعْرُوفِ وَنَهَوْا عَنِ الْمُنكَرِ ۗ وَلِلَّهِ عَاقِبَةُ الْأُمُورِ [٢٢:٤١]

‹‹(እነርሱም) እነዚያ በምድር ላይ ብናስመቻቸው ሶላትን እንደሚገባ የሚያስተካክሉ፣ ዘካንም የሚሰጡ፣ በደግ ነገርም የሚያዝዙ፣ ከመጥፎ ነገርም የሚከለክሉ ናቸው፡፡ የነገሮቹም ሁሉ መጨረሻ ወደ አላህ ነው፡፡ ››

(አልሐጅ 39-40)

የአረብምድርያጥለቀለቀውድልነብዩሰ.ዐ.ወከተላኩበትእስክህልፈታቸውበሀያሶስትአመትውስጥየሚቹ ቁጥርከሙስሊሙምሙስሊምካልሆነውም 375 ወንዶችብቻእንደነበሩታሪክያስረዳናል።

ከነብዩ ሰ.ዐ.ወ እልፈት ቡሃላም ባልደረቦቻቸው ተመሳሳይ ነገር ነበር የፈፀሙት የተለያዩ ሀገራትን በጥሩ ስነ ምግባር ሀላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ግዛታቸውን አስፍፍተዋል።

በሺር አሕመድ ሳድ እስልምና አዲስየተቀበለ ሰው እንዲህ ይላል ። አንድ ጥያቄ ይከነክነኝ ነበር እኛ ክርስትያኖች እስልምና በሰይፍ የተስፋፋ ሃይማኖት ነው እንላለን ።ለምን በተለያየ የአለማችን ክፍል ሰው እስልምና ይቀበላል ተቀብለውም እስከአሁን ይዘውታልአልኩለራሴ ለምንስ ሰው ያለምንም አስገዳጅ ሁኔታ እና ማንኛውም ተፅእኖ ሳይኖር በፍቃደኝነት በየጊዜው ወደሃይማኖቱ ይገባሉ ? እውነት እስልምና ሃይማኖት ብቻ ነው ሀይል በማጠናከርና ራሱን ለመከላከል ያዘዘው ?

በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 20 ቁጥር አስር እና ከሱ ቀጥሎ እንዲህ ይላል፡-

፲ ለመዋጋት ወደ አንዲት ከተማ በደረስህ ጊዜ አስቀድመህ በዕርቅ ቃል ጥራቸው።

፲፩ የዕርቅ ቃልም ቢመልሱልህ ደጅም ቢከፍቱልህ፥ በከተማ ውስጥ ያለው ሕዝብ ሁሉ ይገብሩልህ ያገልግሉህም።

፲፪ የዕርቅ ቃልም ባይመልሱልህ ከአንተም ጋር መዋጋት ቢወድዱ፥ አንተ ከተማይቱን ትከብባለህ ታስጨንቃትማለህ፤

፲፫ አምላክህም እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፎ በሰጣት ጊዜ፥ በእርስዋ ያሉትን ወንዶች ሁሉ በሰይፍ ስለት ትገድላቸዋለህ፤

፲፬ ነገር ግን ሴቶቹንና ሕፃናትን እንስሶቹንም በከተማይቱም ያለውን ምርኮ ሁሉ በዝብዘህ ለአንተ ትወስዳለህ፤ አምላክህም እግዚአብሔር የሚሰጥህን የጠላቶችህን ምርኮ ትበላለህ።

፲፭ የእነዚህ አሕዛብ ከተሞች ባይደሉት ከአንተ እጅግ በራቁት ከተሞች ሁሉ እንዲሁ ታደርጋለህ።

፲፮ ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ከሚሰጥህ ከእነዚህ አሕዛብ ከተሞች ምንም ነፍስ አታድንም።

፲፱ ከተማይቱን ለመውሰድ በመውጋት ብዙ ቀን ከብበህ ባስጨነቅሃት ጊዜ፥ ምሳርህን አንሥተህ ዛፎችዋን አትቍረጥ፤ ከእነርሱ ትበላለህና አትቍረጣቸው፤ ከብበህ የምታጠፋው የምድር ዛፍ ሰው መሆኑ ነውን?

፳ ለመብል የማይሆኑትን የምታውቃቸውን ዛፎች ታጠፋቸዋለህ፥ ትቈርጣቸውማለህ፤ እስክታሸንፋትም ድረስ በምትዋጋህ ከተማ ላይ ምሽግ ትመሽጋለህ።

በኦሪት በዚህ ርዕስ ስር በማቴዎስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 34 — 38 እንዲህ ይላል፡-

፴፬ በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም።

፴፭ ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤

፴፮ ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል።

፴፯ ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤

፴፰ መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም።

፴፱ ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።

ጆስተን ሎብን የአረብ ስልጣኔ በሚለው መፅሃፍ በገፅ 127 —128 ሙስሊሞች ቁርአንን ለማስራጨት የተጠቀሙት ሃይል አልነበረም፡፡ እስልምና ያልተቀበሉት ህዝቦችን በነፃነት ሃይማኖታቸውን እንዲያካይዱ ትተዋቸዋል፡ሃይማኖታቸውን ትተው እስልምና ተቀብለው አረብኛው እንደ ቋንቋቸው የያዙት ህዝቦችም መሪዎቻቸው ላይ ያላዩት ፍትህ በሙስሊም መሪዎች ስላዩና ከዚህ በፊት የማያቁትን ገርነት እስልምና ሃይማኖት ላይ ስላገኙ ነ በር ይላል፡፡

## እውነት በእስልምና የግዛት መስፋፋቱ ሂደት የነበረው ምቶች እና የህዝብሃብት ፍለጋ ነበር?

የእስልምና መሠረታዊ እውቀት የሌለው ሰው  እንዲህ ኣይነቱን አስተሳሰብ አእምረው ላይ ውል ሊልበት ይችላል ብሎም በዚህ ቁሳዊ በሆነ አስተሳሰብ ሊያምን ይችላል፡፡

ነቢዩ ሰ.ዐ.ወመጀመርያ የእስልምና ጥሪ(ዳዕዋ) ማድረግ በጀመሩበት ወቅት ቁረይሾች ጌታ ብለው የሚጠሩትን ዋጋ ሊያሳጣ እና ማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ቦታ ያናጋል ብለው ያሰቡትን የነቢዩ ሰ.ዐ.ወ የእስልምና ጥሪ (ዳዕዋ) ካቆሙ በምትኩ የሚፈልጉትን በሙሉ እንደሚያሟሉ እና የሚጠይቁትን በሙሉ ተፈፃሚ እንደሚሆን እና ሹመት ከሆነ የሚፈልጉት ሊሾምዋቸው፤ ሴት ከሆነ የሚፈልጉት ቆንጆዋን መርጠው ሊድርዋቸው ፤ ብር ከሆነ ደግሞ የሚፈልጉት ሊሰጥዋቸው እንደሚችሉ ምርጫቸውም ለነቢዩ ሰ.ዐ.ወ አቀረቡ፡፡ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ በልበ ሙሉነት(በአላህ ስም እምላለሁ ፀሀይን በቀኝ እጄ ጨረቃን በግራ እጄ አሰቀምጠው ይህንን ሃይማኖት እንድተው ቢያደርጉ አላህ ግልፅ እስኪያዎጣው አልያም እኔ እስክጠፋ አልተወውም) (ኢብን ሂሻም)

ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ የዱንያ ጉጉት እና ዓላማ ለሌለው ነገር ጥሪ አደራጊ ቢሆኑ ኑሮ የቀረበላቸውን ጥያቄ በመመለስ እድሉን ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ነገርግን ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ለሃቅ የተላኩ  ከአፀያፊና አለማዊ ነገር የራቁ ናቸው፡፡

ነቢዩሰ.ዐ.ወ በዙርያቸው ለነበሩ ንጉሶች እና መሪዎች ወደ እስልምና ጥሪ ደብዳቤ ሲልኩ ንግስናቸው ላይ እንዲቆዩና በራሳቸው የሚገኘውን ነገር ሁሉ የራሳቸው እንደሆነ በመግለፅ ጭምር ነው፡፡ከላኩት ደብዳቤ ውስጥ ለታላቁ ሮም (ቤዛንታይን) መሪ የነበረው ሂረቅል የላኩት ደብዳቤ እንይ፡፡ (በአላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ ሩህሩህ በሆነው ከመሐመድ የአላህ መልእክተኛ ወደ ሮም (ቤዛንታይን) ንጉስ ሂረቅል፡ ሰላም ትክክለኛውን መንገድ በተከተለው ላይ ይሁን፡በመቀጠል ወደ እስልምና እጠራሀለሁ፡ ሰላም ታገኛለህ፡ ሰላም አላህ እጥፍ ምንዳን ይሰጠሃል፡እስልምናን ካልተቀበልክ ግንየ ተከታዮችህን(ህዝብህ)ጥፋት ትሸከማለህ፡፡)አላህ እንዲህ ይላል፡-

قُلْ يَا أَهْلَ الْكِتَابِ تَعَالَوْا إِلَىٰ كَلِمَةٍ سَوَاءٍ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ أَلَّا نَعْبُدَ إِلَّا اللَّهَ وَلَا نُشْرِكَ بِهِ شَيْئًا وَلَا يَتَّخِذَ بَعْضُنَا بَعْضًا أَرْبَابًا مِّن دُونِ اللَّهِ ۚ فَإِن تَوَلَّوْا فَقُولُوا اشْهَدُوا بِأَنَّا مُسْلِمُونَ [٣:٦٤]

«የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ፡፡ (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው፡፡ እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው፡፡»
(ኣልዒምራን 64)

**አነስ (ረ.ዐ) ሲናገር ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ የተጠየቁትን በሙሉ ያለ ስስት ይሰጡ እንደነበሩ ገልፀዋል፡ (አንድ ሰው ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ጋር መጥተው በሁለት ተራራ መሃል የሚገመት ፍየል ስጡት ይህም ሰው ወደህዝቡ በመመለስ እስልምናን ተቀበሉ መሀመድ ለድህነት ፍራቻ** የሌላትን አሰጣጥ እየሰጠ ነው በማለት ጥሪ አደረገ ) (ሙስሊም)

አንድ ቀን የነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ባልደረባ የሆነው ዑመር (ረ.ዐ) ወደ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ቤት መጣና አይኑን አንከራትቶ ያየነው ነገር ቢኖር ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ  ጋደም ያሉበት ሰሌን የሰሌኑ ምልክት ም ሰውነታቸው ላይ ይታይ ነበር፡ ሌላው አንድ ቁና ገብስ ነበር፡ ግማሽ የዓረብ ሃገራትን ግዛታቸው ስር ያደረጉት ነብይ ይህ ብቻ ነበር ንብረታቸው፡ ይህንን የተመለከተው ዑመር ራሱን መቆጣጠር አቅቶት እምባውን አምልጦት በጉንጮቹ መሃል ይፈስ ጀመር ፡ ይህንን የተመለከቱ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ምን ያስለቅሰሀል ብልው ጠየቁት ? ዑመርም ለምን አላለቅስም ኪስራ (የፋሪስ ንጉስ) እና ቀይሰር(ቤዛንታይን ንጉስ) በዱንያ ምቾት እና ፀጋ እየኖሩ አንቱ ግን ከማየው ውጭ ምንም ነገር የሉህም አላቸው እሳቸውም ዑመር ሆይ ለኪስራ ና ቀይሰር የዱንያ ፀጋ ለኛ ደግሞ የአኺራ (የመጨረሻይቱ ሀገር ) እንዲሆነን አትሻምን በማለት መለሱለት፡፡

ከነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ህልፈት ቡሃላም ቢናይ ዓምር ቢን ሓሪስ (ረ.ዐ) ሲናገር (ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ሲሞቱ ወርቅም ፤ ጠገራ ብርም፤አገልጋይም ምንም ነገር አልተዉም ከነጭ በቅሏቸው ፤ የጦር መከላከልያቸው እና ለሰደቓ (ምፅዋት) የሰጣት መሬታቸው በስተቀር ) (ቡኻሪ)

ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ሲሞቱ የጦር ልብሳቸው ቤተሰቦቻቸውን  ለመቀለብ በቁና ስንዴ በመያዥነት ተይዞ አንድ የሁዳዊ ጋር ነበር ፡፡ ተመልከቱ የት ያለው የዱንያ ፍቅር የት ያለው የሀብት ፍቅር ነው ፡፡ ሁለተኛው ኸሊፋ ዑመር ቢን ኸጣብ ረ.ዐ ግዛቱ ያለ ቅጥ የተስፋፋ ነበር፡ ሆዱ በረሀብ ድምፅ ሲያሰማ ግን ብትጮህም ባትጮህም በአላህ ስም እምላለሁ ሙስሊሞች እስካልጠገቡ ድረስ አትጠግብም ይል ነበር፡፡

በኡሁድ ጦርነት ጊዜ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ አሉ (ለፍትዋ የሰማይ እና የምድር ወደ ሆነችው ጀነት ቁሙ አሉ ይህንን የሰማው ዑመይር ቢን ሐማም ረ.ዐ ጎሽ አለ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲ እንድትል ያረገህ ምንድነው ? አሉት እሱም በአላህ ስም እምለለሁ እኔም ከሷ እንድሆን ከጅየ ነው አላቸው እሳቸውም አንተ ከሷ ነህ አሉት ፡ የተወሰነ ቴምሮች አውጥቶ መብላት ጀመረ ከዛም እኔንም እኔንን ቴምር እስክበላ በሂወት ከቆየሁማ ረጅም እድሜ ነው በማለት የያዘው ቴምር ጥሎ ወደ ፍልምያውገባ ተዋግቶም ተሰዋ ) (ሙስሊም)

ሙስሊሞች መጀመርያ ላይ የከፈትዋቸው( የተቆጣጠሩት) ሀገራት እነሱን እና ከነሱ ቡሃላ ያለውን ትውልድ በሙቾት እና በድሎት  ማኖር የሚችል ነበር፡ ነገር ግን ከዚህ ድል ጀርባ ለሀይማኖት ጥሪ ማድረግ ለመላው ህዝብ ማድረስ እንጂ ሀብትና የሀገሪቱ ንብረት ለመያዝ አልነበረም፡፡ የግዛት መስፋፋት ዓላማ ዓለማዊ ፍላጎት ለሟሟላት እንዳልነበረ ያሳየናል፡፡ በተቆጣጠሩት ሀገር ለህዝቡ ምርጫ ይሰጡ ነበር ፡ እስልምናውን ከተቀበሉ እንደ ሙስሊሙ የሚገባቸውን መብት እንዳለቸው ፡ ከነሱ የሚጠበቀው ግዴታ እንዳለባቸው እና አንቀበልም ካሉ ደግሞ በሚኖሩበት ሀገር ለሚደረግላቸው የጥበቃ እና የመሳሰሉት አገልግሎት የተወሰነ ግብር እንዲከፍሉ ይገደዳሉ

ይህም ሙስሊሞች ግዴታ የሆነባቸው በየአመቱ ከሚከፍሉት ዘካ እጅጉን ያነሰ ነው ። በዚህ ካልተስማሙ ግን የአላህን ሀይማኖት ለማድረስ ጦርነት ግዴታ ይሆናል፡ ምናልባትም ሀይማኖትን ካወቀ ሊሰልም ይችላል ፡ ሀይማኖቱ ሰዎች ዘንድ እንዳይደርስ መንገድ የሚዘጋ ሁሉ መዋጋት ግዴታ ይሆናል ።

የሙስሊሞች የጦር መሪ የነበረው እስልምና ከመቀበሉ በፊትም ይሁን ቡሃላ ሽንፈትን ያላስተናገደው ጀግናው ኻሊድ ቢን ወሊድ ረ.ዐ ሲሞት ከፈረስ፣ሰይፍ እና አንድ አገልጋይ በስተቀር ምንም ነገር አልነበረውም ፡ ታድያ የት ያለው ዓለማዊ ፍቅር፡ ስሜትን ማዳመጥ እና ሀብትን መውደድ ነው ?

ቀደምት ሙጃሂዶች ፍላጎታቸው ዲኑን ማሰራጨት እንደነበረ ሽዳድ ቢን ሃዲ ረ.ዐ የሚያወራው ሀዲስ ያስረዳናል (አንድ ሰው ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ጋር መጣና ከአንተ ጋር መሰደት እፈልጋለሁ አላቸው እሳቸውም ሰሀቦቻቸውን (ባልደረቦቻቸውን) አደራ አሉ በወቅቱ ጦርነት ላይ የማረክዋቸው ንብረቶች አከፋፍሉ ለሰውየውም የሚገባውን ስጡት ሰውየውም ምንድነው በማለት ጠየቀ ?) ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ያንተ ድርሻ ነው አሉት እሱም ይህንን ፍለጋ እኮ አይደለም በነብይነትህ ያመንኩት (የተከተልኩህ) ነገር ግን በቀስት እዚ.ጋር ተመትቼ በጣቱ ጉሮሮውን እያመላከተ ሞቼ ጀነት እንድገባ ነው አላቸው እሳቸውም አላህ ካመንክው አላህም ያምንሀል አሉ ትንሽ እንደቆዩ ጦርነት ጀመረ ሰዎች ተሸክመው ወደ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ አመጡት እሳቸውም እሱ ነው ? ብለው ጠየቁ አዎ አልዋቸው ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ አላህን አመነ አላህም አመነው ከዛም በ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ከፈን ተከፍኖ ሰገዱበት ሰላታቸው ላይም (ጌታየ ሆይ ይህ ባርያህ ባንተ መንገድ ስደተኛ ሆኖ መጥተዋል ሸሂድ ሁኖም ተገድለዋል እኔም በዚ ላይ መስካሪ ነኝ) (ነሳኢ)

ቀደምት ሙስሊሞች በተመሳሳይ አጋጣሚዎች ዱንያን ረግጠው አለም በቃን ብለውአለማቸው ለሀይማኖት ጥሪ ማድረግ እና እስልምና ሀይማኖት ለሁሉም ሰው አድርሰው በዚህም ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ቃል የገቡትን በመከጀል ነበር(ለአንድ ሰው የሂዳያ(ትክክለኛው መንገድ መምራት)መሆን ከቀይ ግመል(በወቅቱ አረቦች ይሚመፃደቁበት ንብረት)) የተሻለ ነው።

ብዙዎች እስልምና ሀይማኖት ውስጥ ከገቡ ቡሀላ ስልጣናቸውም ንብረታቸውም አጥተዋል ይህም ራሳቸው ንና ቤተሰቦቻቸው ከነዚህ ነገሮች በማራቃቸው አልያም ለሀይማኖቱ ጥሪ ሀሳባቸው እና ጊዛቸውን በመስጠታቸው ነበር ።

በነሃውንድ ጦርነት ታላቁ ሰሃቢይ ኑዕማን ቢን ሙቐረን አልመዝኒይ ያለውን እንመልከት ( ጌታየ ሆይ ሀይማኖትህን ከፍ አድርግ ባሮችህን ድል አጎናፅፍ ኑዕማንንም የዛሬ የመጀመርያው ሸሂድ (የሚሰዋ) አርገው፡ ጌታዬ ሆይ ኣሬ እስልምናን ከፍ በማድረግ አይኔን አርጋልኝ) አላህ ይዘንላቹህና እውነት በዚህ ጥያቄ አለማዊ ፍላጎት ይኖረዋል ? ሙስሊሞች የባቢሎን ምሽግ በከበቡ ጊዜ ዓምር ቢን ዓስ ረ.ዐ ዘንድ መልእክት አድርሶ የተመለሰው የሙቀውቂስ መልእክተኛ ንግግር እንይ (ከመኖር መሞት የሚያስበልጡ፡ ከፍ ከማለት መተናነስ የሚመርጡ ፡ አንዳቸውም የዚች ዓለም ፍላጎት የሌላቸው ፡ አፈር ላይ የሚቀመጡ፡ መሪዎቻቸው ከነሱ የማይለዩ ፡ ትልቃቸው ከትንሻቸው የማይለይ፡ አለቃቸው ከባርያቸው የማይለይ ህዝቦች አየን )

ቶማስ ካርሊል (The carlyle) ጀግኖች በሚለው መፅሀፉ እስልምና በሀይል እና በሰይፍ የተስፋፋ ሀይማኖት ነው ለሚሉት ምላሽ ሲሰጥ ሰይፍ ባይኖር ኑሮ እስልምና ሀይማኖት አይስፋፋም ነበር ይላሉ ፡ ነገር ግን ሰይፍን ያስገኘው ምንድነው? ሀይማኖቱ ጠንካራ የሆነው እውነት ስለያዘና አዲስ አስተሳሳብ ስለሆነ ነው፡ መጀመርያ ሲጀምር በአንድ ሰው ጭንቅላት ውስጥ ነው ይህ እምነት የሚኖረው ይህንን እምነት የያዘ አንድ ግለሰብ የአለም ተቃራኒ ይሆናል ፡ ይህ ግለሰብ

መሳርያ ይዞ አለምን ቢጋፈጣት ደግሞ ይጠፋል፡ በአጠቃላይ እውነት በራሷ በየትኛውም መንገድ ትስፋፋለች ፡ ክርስትና ሀይማኖትም ብናይ አንዳንዴም ቢሆን ሰይፍን ከማንሳት አትቦዝንም ነበር ።እኔም የእውነት ስርጥት በሰይፍ ወይም በንግግር አልያም በተለያየ መንገድ የተሻለ ነው አልልም፡ እውነት ስልጣንዋን እንትታሰራጭ እንተዋት በንግግርም፡ በስምምነትም፡ በእሳትም፡ ጥራ ግራበእጃዋ በእግራም ይሁን በጥፍራ እንድትቋቋም እንተዋት ፡ በፍፁም አትሸነፍም። መሸነፍ ያለበት ካልሆነ በስተቀር።

## የእስልምና መመርያ ከጭካኔ እና ሀይል የራቀ ነው

እስልምና ሀይማኖት የእዝነትና የርህራሄ ለሀይልና ጭካኔ ቦታ የማይሰጥ ነው ። ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ሳሌ በማድረግ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ሲል ይገልፃል

فَبِمَا رَحْمَةٍ مِّنَ اللَّهِ لِنتَ لَهُمْ ۖ وَلَوْ كُنتَ فَظًّا غَلِيظَ الْقَلْبِ لَانفَضُّوا مِنْ حَوْلِكَ ۖ

‹‹ከአላህም በኾነች ችሮታ ለዘብክላቸው፡፡ ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በኾንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር፡ ፡››

(አልዒምራን 159)

የእስልምና ትምህርቶችም እዝነትንና ርህራሄን መሰረት ያደረጉ ናቸው። ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ሲናገሩ (አዛኞች አላህ ይዘንላቸው ፡ በምድር ላይ ላለው እዘኑ ሰማይ ያለው ያዝንላቹሀል ) (ትርሚዝይ) እስልምና ሁሉም ሰው በእዝነት ሊታይ እንደሚገባ እና ከዚህም አልፎ ከጠላት ጋርም ሊተገበር እንደሚገባ የ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ሀዲስ ያስረዳናል#ሙርከኞችን በመልካም ያዛቸው ;

ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ከጠላት ወገን ለተማረኩት ሙርከኞች ይህ ከሆነ ምክራቸው ለሚሰልሙ ደግሞ እንዴት እንደሚሆን አስቡት ፡ እስልምና እዝነት እና ርህራሄ ከሰው ልጅ አልፎ ለእንስሳ ተገቢ እንደሆነ ይገልፃል ፡ አንድ ሰው ለእንስሳ ባሳየው እዝነት፡ ምህረት እና ጀነትን ለማግኘት ምክንያት እንደሆነው ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ በሀዲሳቸው ይነግሩናል#አንድ ሰው መንገድ እየሄደ ዉሃ ጥም ጠናበት ወደ አገኘው ጉድጋድ ገብቶ ውሃ ጠጥቶ ሲወጣ አንድ ውሻ ጭቃ ሲልስ ያያል፡ ይህ ውሻ እኔ የተጠማሁት ያህል ተጠምተዋል ማለት ነውይልና ወደ ጉድጋድ ወርዶ በጫማው ወሀ ሞልቶ አጠጣው አላህም ማረው አሉ; የ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ባልደረቦች ለእንስሳቶች በምናደርገው ነገር ምንዳ አለን ማለት ነው ? በማለት ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ጠየቁ እሳቸውም ሆድ ያረጠበ ሁሉ ምንዳ አለው አሉ ። በተቃራኒው ደግሞ እንስሳት ማሰቃየት የከፋ ቅጣት እንደምያስከትል ከሚከተለው የነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ሀዲስ እንረዳለን (አንድ ሴት ድመት አስረች፡አልቀለበቻት ፡ ወሀ አላጠጣቻት ወይም ደግሞ ለቃት ከመሬት ያገኘችውን እንድትበላ አልፈቀደችላት በዚህ ሰበብ የእሳት ሆናለች ።(ቡኻሪና ሙስሊም )

ነብያዊ አስተምህሮት ለእንስሳ በጣም አዛኝ እና ርህሩህ እንድንሆን ያስተምራል፡ ታድያ እስልምና ለእንስሳት የሚገባው እዝነት እና ርህራሄ ይህን ያህል ከሆነ አላህ ሱ.ወ ከሁሉም ነገር አልቆ የፈጠረው ውድ የሰው ልጅ የሚገባውን እዝነት እና ርህራሄ አስቡት ።

## የእስልምና የጦር አመራር ስርኣት ከጠላት ጋር የሚደረግ ጦርነት ፍትሃዊነት የሞላው ከበደል ነፃ መሆኑን ይገልፅልናል

በእስልምና ውስጥ ጦርነት የሚባለው ነገር ከሙስሊሞች ስሜታዊነት የፀዳ ነው ፡ ይህም በተላያዩ ክህለቶች እራሳቸው በማሳተፋቸው ነበር እንደ ሒሳብ፣ ህክምና ፣ የፈለክ ጥናት፣ የእንጨት ስራ ፣ የህንፃ ጥበብ ፣ ጌጣጌጥ እና የመሳሰሉት ። ለጦርነት እምብዛም ቦታና ግምት አልሰጡትም ነበር በርግጥ ይህ ስህተት ነው ምንም እንኳ ሰላማዊና ሰብአዊነት የሞላው ሰው ወዳድ እና ሰላም ወዳድ ስሜት ቢኖራቸውም ለጠላት እና ዓለማቸው ምድር ላይ ክፋትና ምግባረ ብልሹ ተግባራት ማስፋፋት የሆኑትነን ግምት ውስጥ ማስገባት ነበረባቸው ። ሽብርተኝነት አላህ በቁርአኑ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል

وَأَعِدُّوا لَهُم مَّا اسْتَطَعْتُم مِّن قُوَّةٍ وَمِن رِّبَاطِ الْخَيْلِ تُرْهِبُونَ بِهِ عَدُوَّ اللَّهِ وَعَدُوَّكُمْ

«ለእነሱም ከማንኛውም ኃይልና ከታጀቡ ፈረሶችም የቻላችሁትን ሁሉ በእርሱ የአላህን ጠላትና ጠላታችሁን ሌሎችንም ከእነርሱ በቀር ያሉትን የማታውቋቸውን አላህ የሚያውቃቸውን (መናፍቃን) የምታሸብሩበት ስትኾኑ አዘጋጁላቸው፡፡»(አልአንፈል 60)

በጠንካራ የጦር ዝግጅት ተንኳሹን ማስፈራራት ወይም ማሸበር በላጭ እንደሆነ ቁርአን ውስጥ እናያለን ፡ ማሸበር ወይም ማስፈራራት የሚባለው ግን ሰላማዊ ሰው ሳይነኩ፣ ፍቅር የሌለው፣ በበሽተኛው እና በተጎጂ ስቃይ እና ህመም የማይደሰት ፣ በማች ሬሳ ሳይቀልዱ እና ሙርከኞችን እያሰቃዩ ከመዝናናት ፍፁም የራቀ ነው ። ሰለሓዲን የቀደምት ሙስሊሞች የጦር አዛዥ እና መሪ ሙርከኞችን ያክም ነበር በመሀከላቸው እየዞረም ወሀ ያጠጣቸው ነበር፡ ሆን ተብለው ባልተፈፀሙና አጋጣሚ በደረሰባቸው ያልተለመደ ጉዳት እና ስቃይ ያለቅስ ነበር፡፡

ጦርነት በሙስሊሞች ዘንድ በሀሳብ ደረጃ ውል ብሎ በፍጥነት ፣ በግርግር፣ ባለማስተዋል እና መጨረሻው ቁጭት እና ስቃይን የሚያወርስ ጦርነት ሳይሆን ጥቃትና በደል ለማስወገድ ፍትህና ሰላም ማህበረሰቡ ዘንድ ለማስፈን የሚደረግ ጦርነት ነው ። በመሰረቱ እስልምና ውስጥ ከእስልምና ውጭ ያለው ማህበረሰብ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ሰለማዊና ተመሳስሎ የመኖር ስሜት ያዘለ ነው ። ወደ ሰላም የሚያደርሱ ወይም የሚጠሩ የተለያዩ መንገዶች ተጠቅመው ውጤት ካላመጣ ግን እስልምና ለሚከተሉት 5 ሁኔታዎች ጦርነት ይፈቅዳል(ያዛል)

### 1. ራስን ቤተሰብን እና ሀገርን ለመከላከል የሚደረግ ጦርነት፡

አላህ እንዲህ ይላል ፡-

وَقَاتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ الَّذِينَ يُقَاتِلُونَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوا ۚ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْمُعْتَدِينَ [٢:١٩٠]

‹‹ እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፡፡ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎን አይወድምና፡፡››

(አለበቀራህ 190)

## 2. የተበደለን እና የተጮቆነን ለመርዳት የሚደረግ ጦርነት፡

**ይህ ነው በእስልምና ውስጥ የሰው ልጅ መብት ለመጠበቅ የሚደረግ ጦርነት ፡ አላህ እንዲህ ይላል**

وَمَا لَكُمْ لَا تُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ وَالْمُسْتَضْعَفِينَ مِنَ الرِّجَالِ وَالنِّسَاءِ وَالْوِلْدَانِ الَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا أَخْرِجْنَا مِنْ هَٰذِهِ الْقَرْيَةِ الظَّالِمِ أَهْلُهَا وَاجْعَل لَّنَا مِن لَّدُنكَ وَلِيًّا وَاجْعَل لَّنَا مِن لَّدُنكَ نَصِيرًا [٤:٧٥]

‹‹ በአላህ መንገድና ከወንዶች ከሴቶችና ከልጆችም የኾኑትን ደካሞች እነዚያን፡- «ጌታችን ሆይ! ከዚች ባለቤቶቿ በዳይ ከኾኑት ከተማ አውጣን ከአንተም ዘንድ ለእኛ አሳዳሪን አድርግልን ከአንተ ዘንድም ለእኛ ረዳትን አድርግልን» የሚሉትን (ለማዳን) የማትጋደሉት ለእናንተ ምን አላችሁ?››

(አል ኒሳእ 75 )

3. **እምነት በማጉደል፣** ሰምምነት በማፍረስ መተዳደርያ ደንብን በመጣስ የሚደረግ ጦርነት አላህ እንዲህ ይላል

وَإِن نَّكَثُوا أَيْمَانَهُم مِّن بَعْدِ عَهْدِهِمْ وَطَعَنُوا فِي دِينِكُمْ فَقَاتِلُوا أَئِمَّةَ الْكُفْرِ ۙ إِنَّهُمْ لَا أَيْمَانَ لَهُمْ لَعَلَّهُمْ يَنتَهُونَ [٩:١٢]

«ከቃል ኪዳናቸው በኋላ መሐላዎቻቸውን ቢያፈርሱ፣ ሃይማኖታችሁንም ቢያነውሩ፣ የክህደት መሪዎችን (ከክህደት) ይከለከሉ ዘንድ ተዋጉዋቸው፡፡ እነርሱ ቃል ኪዳን የላቸውምና፡፡»

أَلَا تُقَاتِلُونَ قَوْمًا نَّكَثُوا أَيْمَانَهُمْ وَهَمُّوا بِإِخْرَاجِ الرَّسُولِ وَهُم بَدَءُوكُمْ أَوَّلَ مَرَّةٍ ۚ أَتَخْشَوْنَهُمْ ۚ فَاللَّهُ أَحَقُّ أَن تَخْشَوْهُ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ [٩:١٣]

«መሐላዎቻቸውን ያፈረሱትን መልክተኛውንም ለማውጣት ያሰቡትን ሕዝቦች እነሱ ለመጀመሪያ ጊዜ የጀመሩዋችሁ ሲኾኑ ለምን አትዋጉዋቸውም? ትፈሩዋቸዋላችሁን? ምእምናን እንደ ኾናችሁም አላህ ይበልጥ ልትፈሩት የተገባው ነው፡፡»

(አልተውባህ 12–13)

4. **ከሙስሊሙ ህብረት(ጀመዓ) እርቅና ፍትህ ትተው አፈንግጠው የወጡትን ስርአት ለማስያዝ የሚደረግ ጦርነት** ፡ አላህ እንዲህ ይላል

وَإِن طَائِفَتَانِ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ اقْتَتَلُوا فَأَصْلِحُوا بَيْنَهُمَا ۖ فَإِن بَغَتْ إِحْدَاهُمَا عَلَى الْأُخْرَىٰ فَقَاتِلُوا الَّتِي تَبْغِي حَتَّىٰ تَفِيءَ إِلَىٰ أَمْرِ اللَّهِ ۚ فَإِن فَاءَتْ فَأَصْلِحُوا بَيْنَهُمَا بِالْعَدْلِ وَأَقْسِطُوا ۖ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ [٤٩:٩]

«ከምዕምናንም የኾኑ ሁለት ጭፍሮች ቢጋደሉ በመካከላቸው አስታርቁ፡፡ ከሁለቱ አንደኛይቱም በሌላይቱ ላይ ወሰን ብታልፍ ያችን ወሰን የምታልፈውን ወደ አላህ ትዕዛዝ እስከምትመለስ ድረስ ተጋደሉ፡፡ ብትመለስም በመካከላቸው በትክክል አስታርቁ፡፡ በነገሩ ሁሉ አስተካክሉም፡፡ አላህ አስተካካዮችን ይወዳልና፡፡»

(አል ሑጁራት 9)

5. ***ሀይማኖትን ለመጠበቅ እና ለመከላከል:***የሀይማኖት አስተምህሮ ለህዝብ እንዳይደርስ የሚያግድ፡ አማኙን የሚያሰቃይ እና ወደ እምነቱ መግባት የፈለገውን የሚከለክለውን ለመዋጋት የሚደረግ ጦርነት ምክንያቱም  እስልምና ለሁሉም ህዝብ የሚደረግ ጥሪ ማንኛውም ሰው ሊሰማው ሊያቀው ከሌላው ጥሩ ነገር እና ፍትህ ካገኘበት ወደ ሀይማኖቱ እንዲገባ እንጂ እስልምና ለተወሰኑ ህዝቦች ብቻ የሚደረግ የሀይማኖት ጥሪ አይደለም ፡፡

   ግዛትን ለማስፋፋት ፡ የህዝቡን ሀብት ለመንጠቅ፡ በፀጋው ለመጠቀም እና ውጤቱ ጥፋትና መመሰቃቀል የሆነ የበቀል ጦርነት ፡ ጉልበት እና ሀይል ለማሳየት ጉራን መሰረት ያደረገ ጦርነት እስልምና በጥብቅ ያወግዛል ፡፡ ምክንያቱም እስልምና ውስጥ ጦርነት የሚደረገው ለአላህ ተብሎ ንግግሩን ፡ ሀይማኖቱን ከፍ ለማድረግ እንጂ የነፍስ ወከፍ ስሜትን ለመጠበቅ እና ለአለማዊ ጉዳይ አይደለም ፡፡ አላህ እንዲህ ፡ አላህ እንዲህ ይላል

   وَلَا تَكُونُوا كَالَّذِينَ خَرَجُوا مِن دِيَارِهِم بَطَرًا وَرِئَاءَ النَّاسِ

   «እንደነዚያ ለትዕቢትና ለሰዎች ይዩልኝ ሲሉ ከአላህም መንገድ ለማገድ ከአገራቸው እንደወጡት አትኹኑ፡፡»

   (አል አንፈል47)

## የጦርነት ቁጥጥር ስርአት በእስልምና

እስልምና ሀይማኖት አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር ጦርነትን ፈቅደዋል ከመሆኑም ጋር የራሱ የሆነ ቁጥጥር እና ስርአትአለው ። ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ አሉ (በአላህ ስም፡ በአላህመንገድ ፡ አላህን በካደው ላይ ተዋጉ፡ ተዋጉ ግን አትካዱ(አታታልሉ)፣ አታስመስሉ ህፃናትን አትግደሉ) (ሙስሊም)

ነብዩ ሰ.ዐ.ወተከታይ የመጀመርያ ኸሊፋ(መሪ) አቡበከር ሲዲቅ ረ.ዐ የጦር አዛዦችን ወደ ጦርነት ሲልካቸው 10ነገሮች ተናግረው በሷም ተመሩ (አትካዱ፣ አታጥብቁ፣ አታታልሉ፣ አታስመስሉ፣ ህፃን ልጅ አትግደሉ፣ ሴት ልጅእና አቅመ ደካማ ሽማግሌ እትግደሉ፣ ዘንባባን(የቴምር ዛፍ) አትጨፍጭፉ አታቃጥሉ፣ ፍሬዋ የደረሰ ዛፍአትቁረጡ፣ ለምግብነት ካልሆነ በሬም በግም ፍየልም አትረዱ፡ ከጅሀድ ራሳቸውን ያገለሉ ህዝቦች ታገኛላቹሀእለፍዋቸው ራሳቸውን ወደ ጅሃድ አልመጡም ) የሚል ትእዛዝ ያስተላልፍ ነበር (አጠበሪ)

## ሙርከኛ በእስልምና ያለው ቦታ

ሙርከኛን ማሰቃየት ፣ ማዋረድ፣ ማስፈራራት፣ በነሱ መመሰል፣ ትእግስታቸውን መፈታተን ለሞት እንዲዳረጉምግብና ዉሃ መከልከል እስልምና ይከለክላል ። አላህ እንዲህ ይላል

وَيُطْعِمُونَ الطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا [٧٦:٨]

«ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድኻ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ፡፡»

إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ اللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنكُمْ جَزَاءً وَلَا شُكُورًا [٧٦:٩]

«የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው፡፡ ከእናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም፡፡(አልኢንሳን 8-9)

በተቃራኒው ሙርከኛንማክበር ለነሱም ማዘንና መራራት እንዳለብን እስልምና ያስተምረናል ፡ የሙስዐብ ቢን ዑመይር ረ.ዐ ወንድምየሆነውአቡ ዓዚዝ ቢን ዑመር እንደተናገረው በበድር ጦርነት ጊዜ ጥቂት ሙርከኞች ውስጥ አንዱ ነበርኩ ነብዩሰ.ዐ.ወ ሙርከኞችን አደራ አሉ ይህን የ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ አደራ የተቀበሉ ህዝቦች ምሳ እና እራታቸው ቴምርአድርገው ለኔ ዳቦ ያበሉኝ ነበር ብለዋል ። ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ሙርከኞች እንዲለቀቁ ይፈልጉና ይገፋፉ ነበር። እንዲህም ይሉ ነበር (ሙርከኛን ልቀቁ ፡ የተራበን አብሉ ፡ የታመመን ጠይቁ )(ቡኻሪ)

## በጦርነት ተሸናፊ የሆነው ወገን የሚኖረው ሁኔታ

ገንዘባቸውን መወሰድ ፡ክብራቸውን ዝቅ በማድረግ ፡ማዋረድ፡ ከቀያቸው ማፈናቀል፡ ለጥፋታቸው ሰበብ መሆን፡፡መበቀል የመሳሰሉትን ኢስላም ከልክሎ በተቃራኒው በመስማማት ወደ ጥሩ በማዘዝ ከመጥፎ በመከልከልፍትህንበማንገስ እና እምነታቸውን በማክበር ያዛል፡፡ አላህምበቁርአኑ እንዲህ ይላል

الَّذِينَ إِن مَّكَّنَّاهُمْ فِي الْأَرْضِ أَقَامُوا الصَّلَاةَ وَآتَوُا الزَّكَاةَ وَأَمَرُوا بِالْمَعْرُوفِ وَنَهَوْا عَنِ الْمُنكَرِ ۗ وَلِلَّهِ عَاقِبَةُ الْأُمُورِ [٢٢:٤١]

<<(እነርሱም) እነዚያ በምድር ላይ ብናስመቻቸው ሶላትን እንደሚገባ የሚያስተካክሉ፣ ዘካንም የሚሰጡ፣ በደግ ነገርም የሚያዝዙ፣ ከመጥፎ ነገርም የሚከለክሉ ናቸው፡፡ የነገሮቹም ሁሉ መጨረሻ ወደ አላህ ነው፡፡ ››

(አልሐጅ41)

እምነታቸውንና ሀይማኖታቸውን በነፃነት እንዲያካሂዱ መተው በተቀራኒው ቤተክርትያናቸው ማፍረስ መስቀላቸውመሰበር ክልክል መሆኑን ከሚቀጥለው የነብዩ ሰ.ዐ.ወ ሀዲስ እንማራለን (ሀይማኖታቸውን እንዲያካሂዱ ተዎቸው)ለዚህ ደግሞ ጥሩ አብነት የሚሆነው ዑመር ቢን ኸጣብ ረ.ዐ ኢዬሩሳሌም ሲቆጣጠር ለህዝቦቿ የሰጠውን ነፃነትእንመልከት (በኣላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ እና ሩህሩህ በሆነው ይህ ከአላህ ባርያ የአማኞች መሪ ዑመር ቢንኸጣብ ለእየሩሳሌም ህዝብ የሰጠው ነፃነት ነው፡፡ለነፍሳቸው ፡ ለገንዘባቸው(ንብረታቸው)ለቤተክርስትያናቸው እናለመስቀላቸው ነፃነትን ስጥተዋል በሀይማኖት ላይገደዱ፡ለማናቸውም ጉዳት እንዳይዳረጉ አዘዎል፡፡ ታድያአለማችከተሸናፊ ወገን ጋር ይህን የመሰለ ፍትህ ፡ጥበብ የሞለበት ይቅርባይነትን በታሪክ አሰተናግዳለች?ዑመርየፈለገውን ቅድመ ሁኔታዎች እነሱ ላይ ማሰቀመጥ ይችል ነበር ነገር ግን ፍትህ እና የአላህ ህግና መመርያ ሁሉምህዝብ ላይ መተግበር ስላለበት ነው፡፡ ሀይማኖታቸው የፈቀደለቸው እንዲመገቡ እንዲጠጡ፡ አሳማዎቸቸውላይገደሉ፡አስካሪ መጠጦቻቸው ላይደፍ ማህበራዊ ጉዳያቸውን ትዳርን፡ፍችን ገንዘብ ነክ ነገሮችን በሀይማኖታቸውእና እምነታቸው መሰረት በነፃነት ሊያካሂዱ እስልምና ይፈቅዳል፡፡ዑመር ረ.ወ ድሉ እናግዛቱ የሱ ሆኖ ሳለ ለአሊያ ህዝቦች የሰጠውን የመሳሳይ ነፃነት እንይ (ይህ የአላህ ባርያ የሆነው ዑመርለ አሊያ ህዝቦች የሰጠው ነፃነት ነው፡፡ ለነፍሳቸው ፡ ለንብረታቸው፡ ለቤተክርስትያናቸው፡ለመስቀላቸው፡ ለደካማው፡ለደህነኛው ለተቀሩት ሁሉ ነፃነት ስጥቻለሁ ቤተክርስትየና ቸው ላይቃጠል ወደ መኖርያነትም ላይቀየር በሷእና በቦታዋ በመስቀላቸውበንብረታቸው በገንዘባቸው የሚያስከፍ ነገር ላይደረግ፡በሀይማኖታችው ላይገደዱ እና ማናቸውም ቢሆን ለአደጋ እንዳይጋለጡ )የሚገልፅ ነበር፡፡

## ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ውጭ ያለው ህዝብ በሙስሊሙ ግዛት ውስጥ የሚኖረው ሁኔታ

በ እስልምና የሀገሪቱ ህግና ደንቡን ተቀብሎና አክብሮ የሚኖረው ከሙሰሊሙ ውጭ ያለው ማህበረሰብ ፍትህዊነት በሞላው፡መብታቸው ተጠብቆ እና ቅር ሳይሰኙ እንዲስተናገዱ ቁርአን ያዛል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል

لَّا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُم مِّن دِيَارِكُمْ أَن تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ [٦٠:٨]

«ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡» (አል ሙምተሒናህ 8)

ከነሱ ጋር መልካም ግንኙነት

መፍጠር በጥሩ ሁኔታ ማስተናገድ እና ለነሱ ይጠቅማል የምትለውን ነገር ላይ መስራት እስልምናያበረታታል፡፡ አነስ ረ.ዐ ሲናገር ( ነብዩ ሰ.ዐ.ወ በጣም የሚወድና የሚያከብር አንድ አይሁድ ወጣት መዲና ውስጥ ነበር፡፡እርሳቸውም ያቀርቡታል ይንከባከቡታል በዚህ ሁኔታ ኑሮ ሊሞት ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩት የዓለማት እዝነት መታመሙንሰምተው ለጠይቁት ገቡ፡፡ ከሞት ጋር ሲታገል አገኙት፡ሸሀዳ እንዲል ተማፀኑት ወትሮውንም ለእርሳቸው ክብር ነበረውናሊታዘዛቸው ፈለገ፡፡ግን ደካማ አባቱን ፈራና ዓይኖቹን ወደ እርሱ ልኮ አንከራተተ፡አባቱ እየለመነው መሆኑ ገበውና#አበልቃሲም የሚያዝህን ፉፅም ;በማለት ፈቀዱለት፡፡ የልጁ ገፅታ በደስታ ፈካ፡ፈጥኖም ሸሀዳ (እስልምና ተቀበለ)አደረገ ብዙሳይቆይ ህይወቱአረፈች፡የዓለማቱ እዝነት የሆኑት ነብይ እንዲት ነፍስከጀሀነም በማደናቸው በሀሴት ተፍለቀለቁ፡፡ለአላህምምስጋና አቀረቡ(ኢብን ሒባን)ዓብደላህ ቢን ዑመር ቤት አንድ ፍየል ታረደ ዓብደሊ.ህ ቢን ዑመር ቤታቸው ሲመጡለየሁዳዊው ጎረቤታችን ሰጣችሁት ብለው ደጋግመውጠየቁ፡፡ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ሲናገሩ ስምቻለሁ ጅብሪል በተደጋጋሚ የጎረቤት(መብት)አደራ ሲለኝ አሁን ካሁንውርስ ይገባችዋል ይለኛል ብየ እሰከ ጠረጥር ድረሰ)(ቲርሚዝይ)

## የእስልምናመሰረታዊመመርያሰላምናፍትህንያጠቃልላልእስልምናወደሚከተሉትነጥበችይመራል (ይጠራል)

1. **ለሰው ልጅ ነፍስ ክብር መሰጠት**፡የሰው ልጅ ነፍስ ክቡር እና ዋጋ ሊሰጠው እንደሚገባ እስልምና ያሰተምራል ለዚህም
ነው ሆን ብሎ የሰው ነፍስ ያጠፋን እንዲገደል እስልምና መመርያ የሚያዘው፡፡በስህተት የሰው ነፍስ ያጠፋው ደግሞ
ለሟች ቤተሰብ የገንዘብ ካሳ(ጉማ)እንዲከፍል ይደረጋል ይህ ማለት ግን ቤተሰቡ ላይ ለደረሰው አደጋ መደጎምያ እንዲሆንተፈልጎ እንጂ ይህ ክፍያ ከሰው ልጅ ነፍስ ጋር እኩል ሊሆንም ሊነፃፀርም አይችልም፡፡በተጨማሪ ባርያ ነፃ ማውጣት ፡
ካልቻለ ሁለት ወር አከታትሎ መፆም ይህንን ማድረግ ካልቻለ ደግሞ 60 ድሀዎችን መመገብ ይኖርበታል፡፡እነዚህ ነገሮች ሲሟሉ ብቻ ነው በሰህተት ላጠፋው ነብስ ንስሀ መግባት እና ለጥፋቱ ወደ አላህ ይቅር ባይነቱን ከጅሎ መቃረብ የሚችለው፡፡
ይህ ሁሉ የሚሆነው ውድ የሆነችዋን የሰው ልጅ ነፍስ ለመጠበቅ እና ማንም በነፍስ ወከፍ ነፍስ እንዳይጫወት ለመጠበቅ እና የግድያ ወንጀል እንዳይከሰት ለማገድ ነው፡፡
ምክንያቱም ነፍስ ካጠፋ እንዲሚገደል የሚያቅ ሰው እንደዚ አይነቱን አፀያፊ ድርጊት እና ክፉ ተግባር ከማድርግ ይቆጠባል፡፡ቅጣቱ ይህ ባይሆን ኑሮ ግን ክፋትና ተንኮል አፀያፊ ተግባራትን በሰፊው ይሰራጭ ነበር፡፡

የሰው ልጅ ነፍስ እና መብት ለመጠበቅየእስልምናሀይማኖት ከደነገጋቸው ህጎች ውስጥ ይህኛው በጣም ውጤታማ ሆኖአናገኘዋለን፡፡አላህ እንዲህ ይለል፡-

وَلَكُمْ فِي الْقِصَاصِ حَيَاةٌ يَا أُولِي الْأَلْبَابِ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ [٢:١٧٩]

አንዳችሁን ሞት በመጣበት ጊዜ ሀብትን ቢተው ለወላጆችና ለቅርብ ዘመዶች በበጎ መናዘዝ በናንተ ላይ ተጻፈ፡፡ (ይህ) በጥንቁቆቹ ላይ እርግጠኛ ድንጋጌ ተደነገገ፡፡ (አልበቀራህ179)

ሆን ብሎ የሰው ልጅ ነፍስ ያጠፋው ቅጣት በዚች ምድር (ዱንያ) ብቻ አያበቃም፡፡ ከዚህ የከፋ የመጪው አለም (አኺራ)ብርቱ ቅጣት እና የአላህ ቁጣ እንደሚጠብቀው ቁርአን ይገልፃል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል

وَمَن يَقْتُلْ مُؤْمِنًا مُّتَعَمِّدًا فَجَزَاؤُهُ جَهَنَّمُ خَالِدًا فِيهَا وَغَضِبَ اللَّهُ عَلَيْهِ وَلَعَنَهُ وَأَعَدَّ لَهُ عَذَابًا عَظِيمًا [٤:٩٣]

«ምእመንንም አስቦ የሚገድል ሰው ቅጣቱ በውስጧ ዘውታሪ ሲኾን ገሀነም ናት፡፡ አላህም በርሱ ላይ ተቆጣ፡፡ ረገመውም፡፡ ለእርሱም ከባድ ቅጣትን አዘጋጀ፡፡»

(አል ኒሳዕ 93)

2. **የሰው ልጅ እኩልነት**፡በእስልምና ሀይማኖት የሰው ልጅ ሁሉ ሲፈጠር በተፈጥሮ ወንዱም ሴቱምእኩል ነው ፡፡አላህ እንዲህ ይላል

يَا أَيُّهَا النَّاسُ اتَّقُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَاحِدَةٍ وَخَلَقَ مِنْهَا زَوْجَهَا وَبَثَّ مِنْهُمَا رِجَالًا كَثِيرًا وَنِسَاءً ۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ الَّذِي تَسَاءَلُونَ بِهِ وَالْأَرْحَامَ ۚ

‹‹ እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን ከእርስዋም መቀናጀዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ፡፡ ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ»(አልኒሳዕ1)

ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ አሉ (የሰው ልጅ ከአደም የተገኘ ነው አደም ደግሞ ከአፈር የተገኘ ነው)(አህመድ)ይህንንእኩልነት መሰረት ያደረገው የእስልምና ሀይማኖት ለሰው ልጅ በሙሉ እኩል ነፃነት እንደሚገባው ያስረዳል፡፡ ከ 14 ክፍለ ዘመን በፊት ዑመር ቢን ኸጣብ ረ.ዐ እንዲህ ሲል ተደምጠዋል፡፡(እናቶቻቸው ነፃ የወለደቻቸው ሰዎች እንዴት ባርያ ታረጋላችሁ)

3. **የሀይማኖት አንድነት ፡**

ከነብዩ አደም ጀምሮ እስከ የነብያት መደምደምያ የሆኑት ነብዩ መሀመድ ሰ.ዐ.ወ ከአላህ የወረደላቸው መልዕክት በጥቅሉ አንድ ነው፡፡የሀሉም ነብያቶች ሀይማኖት አንድ አይነት

**ነው። ይህምከአላህ በወረደ መለኮታዊ መፅሀፍ እና መለኮታዊ ራእይ (ወሕይ)አሰተምህሮ መሰረት አላህን በብቸኝነት ማምለክ ነው። አላህ እንዲህ ይላል**

شَرَعَ لَكُم مِّنَ الدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِ نُوحًا وَالَّذِي أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ وَمَا وَصَّيْنَا بِهِ إِبْرَاهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰ ۖ أَنْ أَقِيمُوا الدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُوا فِيهِ ۚ

‹‹ ለእናንተ ከሃይማኖት ያንን በእርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ፡፡ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በእርሱ ኢብራሂምን ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ በእርሱም አትለያዩ ማለትን (ደነገግን)፡፡››

(አልሹራ 13)

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَكُونُوا كَالَّذِينَ آذَوْا مُوسَىٰ فَبَرَّأَهُ اللَّهُ مِمَّا قَالُوا ۚ وَكَانَ عِندَ اللَّهِ وَجِيهًا [٣٣:٦٩]

‹‹ እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እንደእነዚያ ሙሳን እንዳሰቃዩት ሰዎች አትኹኑ፡፡ ካሉትም ነገር ሁሉ አላህ አጠራው፡፡ አላህም ዘንድ ባለሞገስ ነበር፡፡››በሌላ ምዕራፍ (አልአሕዛብ 69)

**ለነብዩ ሙሳ የወረዳው ተውራት (መለከታዊ መፅሀፍ)ወደ ብርሃንና ትክክለኛ መንገድ የሚመራ መሆኑን አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይገልፀዋል**

إِنَّا أَنزَلْنَا التَّوْرَاةَ فِيهَا هُدًى وَنُورٌ ۚ يَحْكُمُ بِهَا النَّبِيُّونَ الَّذِينَ أَسْلَمُوا لِلَّذِينَ هَادُوا وَالرَّبَّانِيُّونَ وَالْأَحْبَارُ بِمَا اسْتُحْفِظُوا مِن كِتَابِ اللَّهِ وَكَانُوا عَلَيْهِ شُهَدَاءَ ۚ فَلَا تَخْشَوُا النَّاسَ وَاخْشَوْنِ وَلَا تَشْتَرُوا بِآيَاتِي ثَمَنًا قَلِيلًا ۚ وَمَن لَّمْ يَحْكُم بِمَا أَنزَلَ اللَّهُ فَأُولَٰئِكَ هُمُ الْكَافِرُونَ [٥:٤٤]

«እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትኾን አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በእነዚያ አይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፡፡ ሊቃውንቱና ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠብቁ በተደረጉትና በርሱም ላይ መስካሪዎች በኾኑት (ይፈርዳሉ)፡፡ ሰዎችንም አትፍሩ፡፡ ፍሩኝም፡፡ በአንቀጾቼም አነስተኛን ዋጋ አትለውጡ፡፡ አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡»(አል ማኢዳህ 44)

**የ ነብዩ ሙሳ ህዝቦች በወቅቱ ከሌሎች የበለጡ እና የተከበሩ ህዝቦች እንደነበሩ አላህ በ ቁርአኑ ገልፆታል**

يَا بَنِي إِسْرَائِيلَ اذْكُرُوا نِعْمَتِيَ الَّتِي أَنْعَمْتُ عَلَيْكُمْ وَأَنِّي فَضَّلْتُكُمْ عَلَى الْعَالَمِينَ [٢:١٢٢]

«የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬንና እኔም በዓለማት ላይ ያበለጥኳችሁ መኾኔን አስታውሱ፡፡»(አልበቐራህ122)

**ነብዩ ዒሳ (እየሱስ)የተከበሩና እና ከአላህ ዘንድ በሆነ በይሁንቃል ወደዚች ምድር መምጣታቸው አላህ በቀርአኑ እንዲህ ሲል ይናገራል፡፡**

إِذْ قَالَتِ الْمَلَائِكَةُ يَا مَرْيَمُ إِنَّ اللَّهَ يُبَشِّرُكِ بِكَلِمَةٍ مِّنْهُ اسْمُهُ الْمَسِيحُ عِيسَى ابْنُ مَرْيَمَ وَجِيهًا فِي الدُّنْيَا وَالْآخِرَةِ وَمِنَ الْمُقَرَّبِينَ [٣:٤٥]

መላእክት ያሉትን (አስታውስ)፡- «መርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በኾነው ቃል ስሙ አልመሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ ከባለሟሎችም በኾነ (ልጅ) ያበስርሻል፡፡»

وَيُكَلِّمُ النَّاسَ فِي الْمَهْدِ وَكَهْلًا وَمِنَ الصَّالِحِينَ [٣:٤٦]

«በሕፃንነቱና በከፈኒሳነቱ ሰዎቹን ያነጋግራል፡፡ ከመልካሞቹም ነው» (አላት)፡፡»(አልዒምራን 45)

**ሰለ እናታቸው መርየም ታማኝነት እና ንፅህናም አላህ እንዲህ ይላል**

مَّا الْمَسِيحُ ابْنُ مَرْيَمَ إِلَّا رَسُولٌ قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِهِ الرُّسُلُ وَأُمُّهُ صِدِّيقَةٌ ۖ كَانَا يَأْكُلَانِ الطَّعَامَ ۗ انظُرْ كَيْفَ نُبَيِّنُ لَهُمُ الْآيَاتِ ثُمَّ انظُرْ أَنَّىٰ يُؤْفَكُونَ [٥:٧٥]

«የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፡፡ (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤ አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት ከዚያም (ከእውነት) እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት፡፡»(አልማኢዳ 75)

**ታዉራት እንደገለፀው ኢንጅል (ለነብዩ ዒሳ (እየሱስ) የወረደ መለከታዊ መፅሀፍ)ወደ ብርሃንና ትክክለኛ መንገድ የሚመራ መሆኑን አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል**

ثُمَّ قَفَّيْنَا عَلَىٰ آثَارِهِم بِرُسُلِنَا وَقَفَّيْنَا بِعِيسَى ابْنِ مَرْيَمَ وَآتَيْنَاهُ الْإِنجِيلَ وَجَعَلْنَا فِي قُلُوبِ الَّذِينَ اتَّبَعُوهُ رَأْفَةً وَرَحْمَةً وَرَهْبَانِيَّةً ابْتَدَعُوهَا مَا كَتَبْنَاهَا عَلَيْهِمْ إِلَّا ابْتِغَاءَ رِضْوَانِ اللَّهِ فَمَا رَعَوْهَا حَقَّ رِعَايَتِهَا ۖ فَآتَيْنَا الَّذِينَ آمَنُوا مِنْهُمْ أَجْرَهُمْ ۖ وَكَثِيرٌ مِّنْهُمْ فَاسِقُونَ [٥٧:٢٧]

«ከዚያም በዱካዎቻቸው ላይ መልክተኞቻችንን አስከታተልን፡፡ የመርየምን ልጅ ዒሳንም አስከተልን፡፡ ኢንጂልንም ሰጠነው፡፡ በእነዚያም በተከተሉት (ሰዎች) ልቦች ውስጥ መለዘብንና እዝነትን፣ አዲስ የፈጠሩዋትንም ምንኩስና አደረግን፡፡ በእነርሱ ላይ (ምንኩስናን) አልጻፍናትም፡፡ ግን የአላህን ውዴታ ለመፈለግ ሲሉ (ፈጠሩዋት)፡፡ ተገቢ አጠባበቋንም፤ አልጠበቋትም፡፡ ከእነርሱም ለእነዚያ ላመኑት ምንዳቸውን ሰጠናቸው፡፡ ከእነርሱም ብዙዎቹ አመጸኞች ናቸው፡፡ ››(አልሐዲድ 27)

**በሁሉም ነብያትና መልዕክተኞች ማመን እና ከአላህ በወረዳው መለኮታዊ መፅሀፍ ማመን የእያንዳንዱ ሙስሊም ግዴታነው፡፡አላህ እንዲህ ይላል**

إِنَّ الَّذِينَ يَكْفُرُونَ بِاللَّهِ وَرُسُلِهِ وَيُرِيدُونَ أَن يُفَرِّقُوا بَيْنَ اللَّهِ وَرُسُلِهِ وَيَقُولُونَ نُؤْمِنُ بِبَعْضٍ وَنَكْفُرُ بِبَعْضٍ وَيُرِيدُونَ أَن يَتَّخِذُوا بَيْنَ ذَٰلِكَ سَبِيلًا [٤:١٥٠]

«እነዚያ በአላህና በመልክተኞቹ የሚክዱ፣ በአላህና በመልክተኞቹም መካከል መለየትን የሚፈልጉ፣ «በከፊሉም እናምናለን በከፊሉም እንክዳለን» የሚሉ፣ በዚህም መካከል መንገድን ሊይዙ የሚፈልጉ፤»

أُولَٰئِكَ هُمُ الْكَافِرُونَ حَقًّا ۚ وَأَعْتَدْنَا لِلْكَافِرِينَ عَذَابًا مُّهِينًا [٤:١٥١]

«እነዚያ በውነት ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡ ለከሓዲዎችም አዋራጅን ቅጣት አዘጋጅተናል፡፡»(አልኒሳዕ 150-151)

**ለሁሉም ነብያቶች ለህዝባቸው በ ተላከው እስላማዊ ህግ እና መመርያ ማክበር እና ከህዝቡ ጋርም ያለው ግንኙነት መለከታዊ እምነት ላይ የተገነባ በመሆኑ እሰላማዊ መወዳጀትን ወንድማማችነትን መኖሩ ከነብዩ ሰ.ዐ.ወ ተልዕኮ በፊት የነበሩ ህዝቦች መሆናቸውን ማመን ግዴታ ይሆናል፡፡አላህ እንዲህ ይላል**

مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَا أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ اللَّهِ وَخَاتَمَ النَّبِيِّينَ ۗ

‹‹ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፡፡ ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፡፡››

(አል አሕዛብ 40)

ለነብዩ ሰ.ዐ.ወ የወረደው እስላማዊ ህግጋት (አስተምህሮ)ከነብዩ ሰ.ዐ.ወ በፊት የ ነበረውን የነብያቶች ህግጋት ሽረዋል፡፡ይህ ማለት ግን ህጉን ማስተባበል ሳይሆን ህጉን ተፈፃሚ ሳያዳርጉ ከነብዩ ሰ.ወ.ዐ በፊት ለነበሩ በሀቅ የተለካ መሆኑ ማመን ነው፡፡አላህ እንዲህ ይላል

فَإِنْ آمَنُوا بِمِثْلِ مَا آمَنتُم بِهِ فَقَدِ اهْتَدَوا ۖ وَّإِن تَوَلَّوْا فَإِنَّمَا هُمْ فِي شِقَاقٍ ۖ فَسَيَكْفِيكَهُمُ اللَّهُ ۚ وَهُوَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ [٢:١٣٧]

‹‹በርሱ ባመናችሁበት ብጤ ቢያምኑ በእርግጥ ተመሩ፡፡ ቢዞሩም እነርሱ በጭቅጭቅ ውስጥ ብቻ ናቸው፡፡ እነርሱንም አላህ ይበቃሃል፤ እርሱም ሰሚው ዐዋቂው ነው፡፡››

إِنَّ الَّذِينَ فَرَّقُوا دِينَهُمْ وَكَانُوا شِيَعًا لَّسْتَ مِنْهُمْ فِي شَيْءٍ ۚ إِنَّمَا أَمْرُهُمْ إِلَى اللَّهِ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم بِمَا كَانُوا يَفْعَلُونَ [٦:١٥٩]

‹‹እነዚያ ሃይማኖታቸውን የለያዩ አሕዛብም የኾኑ በምንም ከእነሱ አይደለህም፡፡ ነገራቸው ወደ አላህ ብቻ ነው፡፡ ከዚያም ይሠሩት የነበሩትን ሁሉ ይነገራቸዋል፡፡››

مَن جَاءَ بِالْحَسَنَةِ فَلَهُ عَشْرُ أَمْثَالِهَا ۖ وَمَن جَاءَ بِالسَّيِّئَةِ فَلَا يُجْزَىٰ إِلَّا مِثْلَهَا وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ [٦:١٦٠]

«በመልካም ሥራ የመጣ ሰው ለእርሱ ዐሥር ብጤዎችዋ አሉት፡፡ በክፉ ሥራም የመጣ ሰው ብጤዋን እንጅ አይመነዳም፡፡ እነርሱም አይበደሉም፡፡»

قُلْ إِنَّنِي هَدَانِي رَبِّي إِلَىٰ صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ دِينًا قِيَمًا مِّلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا ۚ وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ [٦:١٦١]

««እኔ ጌታዬ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትክክለኛን ሃይማኖት ወደ እውነት አዘንባይ ሲኾን የአብርሃምን መንገድ መራኝ፡፡ እርሱም ከአጋሪዎቹ አልነበረም» በል፡፡»

(አል አንዓም 159-160-161)

**የእስልምና ሀይማኖት መመርያ ከሌሎች የሀይማኖት እምነት ተከተዩች ጋር ስትከተለው የነበረው አቋም ወይይትን ነው፡፡የዚህም ወይይት ዓላማ አላህ ወደ አዘዘው ወደ ጥሩ ሰነምግባር የምትጠራዋን የፈጣሪ እምነት እንድንመጣ ነው፡፡አላህም እንዲህ ይላል**

قُلْ يَا أَهْلَ الْكِتَابِ تَعَالَوْا إِلَىٰ كَلِمَةٍ سَوَاءٍ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ أَلَّا نَعْبُدَ إِلَّا اللَّهَ وَلَا نُشْرِكَ بِهِ شَيْئًا وَلَا يَتَّخِذَ بَعْضُنَا بَعْضًا أَرْبَابًا مِّن دُونِ اللَّهِ ۚ فَإِن تَوَلَّوْا فَقُولُوا اشْهَدُوا بِأَنَّا مُسْلِمُونَ [٣:٦٤]

«የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ፡፡ (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው፡፡ እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው፡፡»

(አል ዒምራን 64)

**የሌላ እምነት ተከታዮች ስሜታቸውን መጠበቅ እና ሀይማኖታቸው እና እምነታቸውን ከማንቋሸሽ መቆጠብ እንዳለብን እስልምና ያሰተምረናል፡፡አላህ እንዲህ ይላል**

وَلَا تَسُبُّوا الَّذِينَ يَدْعُونَ مِن دُونِ اللَّهِ فَيَسُبُّوا اللَّهَ عَدْوًا بِغَيْرِ عِلْمٍ ۗ

«እነዚያንም ከአላህ ሌላ የሚገዙዋቸውን (ጣዖታትን) አትስደቡ፡፡ ድንበርን በማለፍ ያለዕውቀት አላህን ይሰድባሉና፡፡»

(አል አንዓም 108)

ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋር መልካም ከሆነችዋ ውይይት ውጭ መከራከርም መጨቃጨቅም እንዳሌለብን አላህ በቁርአኑ ይነገረናል

وَلَا تُجَادِلُوا أَهْلَ الْكِتَابِ إِلَّا بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ إِلَّا الَّذِينَ ظَلَمُوا مِنْهُمْ ۖ وَقُولُوا آمَنَّا بِالَّذِي أُنزِلَ إِلَيْنَا وَأُنزِلَ إِلَيْكُمْ وَإِلَٰهُنَا وَإِلَٰهُكُمْ وَاحِدٌ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ [٢٩:٤٦]

‹‹የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፡፡ ከእነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፡፡ በሉም «በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደናንተም በተወረደው አመንን፡፡ አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፡፡ እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን፡፡»

ادْعُ إِلَىٰ سَبِيلِ رَبِّكَ بِالْحِكْمَةِ وَالْمَوْعِظَةِ الْحَسَنَةِ ۖ وَجَادِلْهُم بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ ۚ

‹‹ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በለዘብታ ቃል) ጥራ፡፡ በዚያችም እርሷ መልካም በኾነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው፡፡››

(አል ነሕል 125)

ከዚ በፊት እንደተጠቀሰው ወደ እስልምና ሀይማኖት እንዲገቡ ማስገደድ ከእስልምና መመርያ ውጭ ነው፡፡አላህ እንዲህ ይላል

ምክንያቱም የእስልምና መመርያ የሚያዘው ያለ ማስጨነቅ ወይም ያለ ማስገደድ እስልምና እንዲያዩ ማድረግ ነው እንጂ ትክክለኛው መመራት እማ በአላህ ሱ.ወ እጅ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል ፡-

وَقُلِ الْحَقُّ مِن رَّبِّكُمْ ۖ فَمَن شَاءَ فَلْيُؤْمِن وَمَن شَاءَ فَلْيَكْفُرْ ۚ إِنَّا أَعْتَدْنَا لِلظَّالِمِينَ نَارًا أَحَاطَ بِهِمْ سُرَادِقُهَا ۚ وَإِن يَسْتَغِيثُوا يُغَاثُوا بِمَاءٍ كَالْمُهْلِ يَشْوِي الْوُجُوهَ ۚ بِئْسَ الشَّرَابُ وَسَاءَتْ مُرْتَفَقًا [١٨:٢٩]

««እውነቱም ከጌታችሁ ነው፡፡ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ» በላቸው፡፡ እኛ ለበደለኞች አጥሯ በእነሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል፡፡ (ከጥም) እርዳታንም ቢፈልጉ እንደ ዘይት ዝቃጭ ባለ ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ ይረዳሉ፡፡ መጠጡ ከፋ! መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች!»

(አልከህፍ 29)

**የእስልምና ሀይማኖት ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ውጭ ያለው ጋር ጭምር በሁሉም ነገር ፍትሀዊ መሆኑን አላህ በቁርአኑ እንዲህ ገልፆታል**

وَأُمِرْتُ لِأَعْدِلَ بَيْنَكُمُ ۖ اللَّهُ رَبُّنَا وَرَبُّكُمْ ۖ لَنَا أَعْمَالُنَا وَلَكُمْ أَعْمَالُكُمْ ۖ لَا حُجَّةَ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمُ ۖ اللَّهُ يَجْمَعُ بَيْنَنَا ۖ وَإِلَيْهِ الْمَصِيرُ [٤٢:١٥]

«በመካከላችሁም ላስተካክል ታዘዝኩ፡፡ አላህ ጌታችን ጌታችሁም ነው፡፡ ለእኛ ሥራዎቻችን አልሉን፡፡ ለእናንተም ሥራዎቻችሁ አልሏችሁ፡፡ በእኛና በእናንተ መካከል ክርክር የለም፡፡ አላህ በመካከላችን ይሰበስባል፡፡ መመለሻም ወደእርሱ ብቻ ነው፡፡»

(አልሹራ 15)

4. **ህብረተሰቡ ተረዳድተው**፡ ተሰባሰበው እና ተዛዝነው የሚፈጥሩት ምቹ እና የተረጋጋ የኑሮ ሁኔታ እና የጋራ ጥቅሞችን እውን ማድረግን እስልምና ሀይማኖት ያበረታታል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል

وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَىٰ ۖ وَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ ۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ ۖ إِنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعِقَابِ [٥:٢]

«በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡ ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ፡፡ አላህንም ፍሩ፡ ፡ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና፡፡»(አል ማኢዳህ 2)

## እስልምና የሚከተሉትን ግቦች ለማሳካት

- የፊጣሪን የነብይ እና ቁርአን መመርያ መሰረት ያደረግ የሕዝብ ግንኙነት እና ትውውቅ እስልምና ያበረታታል፡፡አላህ እንዲህ ይላል

يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا ۚ إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ ۚ

«እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡»(አልሑጅራት 13)

በጎ ስራ መስራት መገፋፋት፡ዓሊ ቢን ሑስይን (ረ.ዐ)ባወሩት ፡ለሁሉም ህዝብ መልካም ነገር ማሰብ እና መውደድ አቡሁረይራ ባወሩት ሀዲስ (ይህንን ንግግር ከኔ የወሰደ ይሰራበት ወይም ለሚሰራበት ሰው ይንገረው(አቡ ሀረይራ እኔ አልኩኝ እጄን ይዘው አምስት ነገር ቆጠሩ፡አላህ የከለከለውን ተከልከል ጥሩ ባርያ ትሆናለህ፡ አላህ በወሰነልህ ነገር ደስተኛ ሁንህብታም ትሆናለህ ፡ ለጎረቤትህ መልካም ሁን አማኝ ትሆናለህ ፡ ለራስህ የምትወደውን ነገር ለሌላውም ሰው ውደድ ሙስሊም ትሆናለህ ፡ ሳቅ አታብዛ ሳቅ ማብዛት ቀልብ ትገላለች ) (ቲርሚዝይ)

- **ለሁሉም ህዝብ ምክር መለገስ** ፡ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ሲናገሩ (ሀይማኖት ምክክር ነው አሉ ለማን አልናቸው ? ለአላህ፣ ለቁርአን፣ ለመልእክተኛ ፣ ለሀይማኖት መሪ እና ለተቀረው ህዝብ (ሙስሊም))
- በተገኘው አጋጣሚ እና ሁኔታ በሚችለው መንገድ ሁሉ በጥሩ ማዘዝ ከመጥፎ መከልከል ምክንያቱም ግፍ እና ምግባር ብልሹነት እንዳይሰራጭ መብቶች እንዳይጣሱ አረመናዊ ህጎች እንዳይስፋፍ የህዝቡን ደህነት መቆጣጠርያ በመሆኑ ነው፡፡በጥሩ ማዘዝ ከመጥፎ መከልከል የማያቀው እንዲያቅ፡የዘነጋው እንዲነቃ፡ ያጠፋው እንዲቀጣ እና ትክክለኛ የሆነው ደግሞ እንዲበረታታ ያግዛል፡፡ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ሲናገሩ (ከናንተ መልካም ያልሆነ ባየ ጊዜ በእጁ ይቀይር ካልቻለ በምላሱ ያውግዝ ካልቻለ በቀልቡ (ይጥላ)ይህ ግን ዝቀተኛ ኢማን ነው(ሙስሊም)
- እወቀትን መሻት እና መማር እስልምና ይገፋፍል፡፡አላህ እንዲህ ይለል ፡-

قُلْ هَلْ يَسْتَوِي الَّذِينَ يَعْلَمُونَ وَالَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ ۗ

«እነዚያ የሚያውቁና እነዚያ የማያውቁ ይስተካከላሉን?» በላቸው፡፡»(አልዙመር 9)

ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንደተናሩት(እውቀትን መፈለግ በሁሉም ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው) ይህም እያንዳንዱ ሙስሊም ከሱ የሚጠበቀውን ግዴታ እና የተሰጠውን መብት አውቆለሌላው ለራሱም እረፍት እንዲያገኝ ይረደዋል፡፡

- አከባበቢን እና የአከባቢ ንብረቶችን(ይዞቶች)መጠበቅ፡
  የነብዩ ሰ.ዐ.ወ አስተምህሮ በአከባቢ የሚገኝ ለሰው ልጅ የሚጠቅም ንብረት ሁሉ ማባከን፣ ማበላሸት ያወግዛል፡በምድር ላይ ያለው ሀብት ሁሉ ንብረትነቱ ወይም ባለቤትነቱ ለሀሉም ህዝብ ነው እንጂ ለተወሰኑ ህብረተሰብ ብቻ አይደለም፡፡ለአከባቢ

**ለመበላሸት ምክንያት የሚሆን ድርጊት ሁሉ መፈፀም እስላም ይከለክላል፡፡አላህ በቁርአኑ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡፡**

وَلَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَاحِهَا وَادْعُوهُ خَوْفًا وَطَمَعًا ۚ إِنَّ رَحْمَتَ اللَّهِ قَرِيبٌ مِّنَ الْمُحْسِنِينَ [٧:٥٦]

«በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ፡፡ ፈርታችሁና ከጅላችሁም ተገዙት፡፡ የአላህ ችሮታ ከበጎ አድራጊዎች ቅርብ ነውና፡፡»

وَإِذَا تَوَلَّىٰ سَعَىٰ فِي الْأَرْضِ لِيُفْسِدَ فِيهَا وَيُهْلِكَ الْحَرْثَ وَالنَّسْلَ ۗ وَاللَّهُ لَا يُحِبُّ الْفَسَادَ [٢:٢٠٥]

«(ካንተ) በዞረም ጊዜ በምድር ላይ በውስጧ ሊያበላሽና አዝመራንና እንስሳዎችን ሊያጠፋ ይሮጣል፡፡ አላህም ማበላሸትን አይወድም፡፡ »

وَإِذَا قِيلَ لَهُ اتَّقِ اللَّهَ أَخَذَتْهُ الْعِزَّةُ بِالْإِثْمِ ۚ فَحَسْبُهُ جَهَنَّمُ ۚ وَلَبِئْسَ الْمِهَادُ [٢:٢٠٦]

«ለእርሱ «አላህን ፍራ» በተባለም ጊዜ፤ ትዕቢቱ በኃጢአት (ሥራ) ላይ ትገፈፋዋለች፡፡ ገሀነምም በቂው ናት፤ (እርሷም) በእርግጥ የከፋች ምንጣፍ ናት፡፡»
(አል በቀራህ 205-206)

- **ምድር ላይ መንቀሳቀስ እና ምድር ለሁሉም በሚመች መልኩ ምቹ ማድረግ፡አላህ እንዲህ ይላል**

هُوَ الَّذِي جَعَلَ لَكُمُ الْأَرْضَ ذَلُولًا فَامْشُوا فِي مَنَاكِبِهَا وَكُلُوا مِن رِّزْقِهِ ۖ وَإِلَيْهِ النُّشُورُ [٦٧:١٥]

«እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው፡፡ በጋራዎቿዋና በመንገዶቿዋም ኺዱ፡፡፡ ከሲሳዩም ብሉ፡፡ (ኋላ) መመለሻውም ወደእርሱ ብቻ ነው፡፡»

(አል ሙልክ 15)

- *አሰካሪ እና አደንዛዥ ዕፅ ለመዋጋት*
  **አላህ እንዲህ ይላል**

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنَّمَا الْخَمْرُ وَالْمَيْسِرُ وَالْأَنصَابُ وَالْأَزْلَامُ رِجْسٌ مِّنْ عَمَلِ الشَّيْطَانِ فَاجْتَنِبُوهُ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ [٥:٩٠]

*«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፡፡ (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና፡፡»*

(አልማኢዳህ 90)

- *ገንዘብ እና ንብረት ለመጠበቅ*
  **አላህ እንዲህ ይላል**

وَلَا تَقْرَبُوا الزِّنَا ۖ إِنَّهُ كَانَ فَاحِشَةً وَسَاءَ سَبِيلًا [١٧:٣٢]

*«ዝሙትንም አትቅረቡ፡፡ እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና፡፡ መንገድነቱም ከፋ!»*

وَالَّذِينَ يَرْمُونَ الْمُحْصَنَاتِ ثُمَّ لَمْ يَأْتُوا بِأَرْبَعَةِ شُهَدَاءَ فَاجْلِدُوهُمْ ثَمَانِينَ جَلْدَةً وَلَا تَقْبَلُوا لَهُمْ شَهَادَةً أَبَدًا ۚ وَأُولَٰئِكَ هُمُ الْفَاسِقُونَ [٢٤:٤]

*«እነዚያም ጥብቆችን ሴቶች (በዝሙት) የሚሰድቡ ከዚያም አራትን ምስክሮች ያላመጡ ሰማኒያን ግርፋት ግረፏቸው፡፡ ከእነርሱም ምስክርነትን ሁልጊዜ አትቀበሉ እነዚያም እነሱ አመጸኞች ናቸው፡፡»*(አልኑር 4)

**በህዝቡ ዘንድ አፀያፊ ተግባራትን ለማስራጨት ፍላጎት ያለው አሳማሚ ቅጣት እንዲሚጠብቀው ይነግረናል፡፡ አፀያፊ ተግባር ለማሰራጨት የተራራጠ ፡መንገድዋ ያገራ ፡ እንዲሰራጭ ያገዘ ደግሞ ቅጣቱ ምን ሊሆን እንዲሚችል አሰቡት፡፡አላህ እንዲህ ይላል**

إِنَّ الَّذِينَ يُحِبُّونَ أَن تَشِيعَ الْفَاحِشَةُ فِي الَّذِينَ آمَنُوا لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ فِي الدُّنْيَا وَالْآخِرَةِ ۚ وَاللَّهُ يَعْلَمُ وَأَنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ [٢٤:١٩]

«እነዚያ በእነዚያ ባመኑት ሰዎች ውስጥ መጥፎ ወሬ እንድትስፋፋ የሚወዱ ለእነሱ በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ዓለም አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡ አላህም ያውቃል እናንተ ግን አታውቁም፡፡»

(አልኑር 19)

**በሰው ሀቅ ገንዘብ ደግሞ አላህ በቀርአኑ እንዲህ ይላል**

وَأَوْفُوا الْكَيْلَ إِذَا كِلْتُمْ وَزِنُوا بِالْقِسْطَاسِ الْمُسْتَقِيمِ ۚ ذَٰلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلًا [١٧:٣٥]

በሰፈራችሁም ጊዜ ስፍርን ሙሉ፡፡ በትክክለኛው ሚዛንም መዝኑ፡፡ ይህ መልካም ነገር ነው፡፡ መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَذَرُوا مَا بَقِيَ مِنَ الرِّبَا إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ [٢:٢٧٨]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፡፡ ከአራጣም የቀረውን ተዉ፡፡ አማኞች እንደኾናችሁ (ተጠንቀቁ)፡፡ »

فَإِن لَّمْ تَفْعَلُوا فَأْذَنُوا بِحَرْبٍ مِّنَ اللَّهِ وَرَسُولِهِ ۖ وَإِن تُبْتُمْ فَلَكُمْ رُءُوسُ أَمْوَالِكُمْ لَا تَظْلِمُونَ وَلَا تُظْلَمُونَ [٢:٢٧٩]

«(የታዘዛችሁትን) ባትሠሩም ከአላህና ከመልክተኛው በኾነች ጦር (መወጋታችሁን) ዕወቁ፡፡ ብትጸጸቱም ለእናንተ የገንዘቦቻችሁ ዋናዎች አሏችሁ፡፡ አትበድሉም አትበደሉምም፡፡»(አልበቀራህ 278)

- **ለህዝብ ደህንነት መቆም እንዲሁም ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ**
- **ወላጅ አልባ ለሆኑትና ቤተሰብ ለሌላቸው የሚደረግ የእርዳታ ጥሪ ፡ አላህ እንዲህ ይላል**

وَلَا تَقْرَبُوا مَالَ الْيَتِيمِ إِلَّا بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ

«የየቲምንም ገንዘብ የብርታቱን ጊዜ እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በኾነች ኹኔታ እንጂ አትቅረቡ፡፡»(አልኢስራዕ 34)

**ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህይላሉ (እኔና ወላጅ አልባ (የቲም)ጧሪ እንደዚህ ነን አሉ ሁለት ጣታቸውን አያመለከቱ)**

- **በተገኘው አጋጣሚ እና ሁኔታ ረሀብን ለመዋጋት የሚደረግ ጥሪ፡ አለህ እንዲህ ይላል**

فَلَا اقْتَحَمَ الْعَقَبَةَ [٩٠:١١]

«ዓቀበቲቱንም አልወጣም፡፡»

وَمَا أَدْرَاكَ مَا الْعَقَبَةُ [٩٠:١٢]

«ዓቀበቲቱም (መውጣቷ) ምን እንደኾነች ምን አሳወቀህ?»

فَكُّ رَقَبَةٍ [٩٠:١٣]

«(እርሱ) ጫንቃን መልቀቅ ነው፡፡»

أَوْ إِطْعَامٌ فِي يَوْمٍ ذِي مَسْغَبَةٍ [٩٠:١٤]

«ወይም የረኃብ ባለቤት በኾነ ቀን ማብላት፡፡»

(አልበለድ 12-14)

- **ባርያን ነፃ እንደያወጡ መገፍፍት፡ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንዳሉት ፡-ባርያን ነፃ ያወጣ ሰው አላህ (ሱወ) ዕያንዳነዱን አካሉን(በሪያውን ነጻ ባወጣበት) አላህ ነጻ ያወጣለታል፡፡ ብልቱንም እንክዋን በዛኛው ሰው ብልት እንክዋን ያወጣለታል፡፡**

## የእስልምና ስነ ምግባር ወደ ሰላም የሚጠራ ነው

የእሰልምና ሰነምግባር ማህበረሰቡ ሁሉ ደሰታ እንዲጎናፀፍ እና ህብረተሰቡ ዘንድ ፀብንና ጥላቻየሚያነሱ ነገሮችን ይከለክላል፡፡ ይህ ተግባር ደግሞ በህብረተሰቡ ዘንድ በቁርጠኝነት ሰላምና እና ድህንነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይጨወታል፡፡የእስልምና ሰነ ምግባር ብዙ ነውዋና መሳርያ ግን ማንኛውም የሚጎዳ ነገር በድርጊትም ይሁን በንግግር በጠቃላይ የሰውን ልጅ ለጉዳት የሚያጋልጥ ሁሉ መጥፎ ሰነ ምግባር ሲሆን አላህም የሚጠላው ነው፡፡ይህን የማይቀበል ሁሉ በዚች ዓለም(ዱንያ)በሰዎች ዘንድ ጥላቻን ያተርፍል፡ በመጨረሻይቱም አገር (አኺራ) ከአላህ ቅጣት የተጋለጠይሆናል፡፡ለዚህም አላህ ሱ.ወ የፍትህ መጋደልና ጭቆናን ከልክለዋል፡፡በጠቃላይ በድርጊትም በንግግርም ሌላውን ማሰከፋት እና ሀቅን መንካት ክልክል ሰለመሆኑ አለህ በቀርአኑ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል

قُلْ إِنَّمَا حَرَّمَ رَبِّيَ الْفَوَاحِشَ مَا ظَهَرَ مِنْهَا وَمَا بَطَنَ وَالْإِثْمَ وَالْبَغْيَ بِغَيْرِ الْحَقِّ

««ጌታዬ እርም ያደረገው መጥፎ ሥራዎችን፣ ከርሷ የተገለጸውንና የተደበቀውን ኃጢኣትንም፣ ያላግባብ መበደልንም፣»(አል አዕራፍ 33)

አላህ በሀዲስ አልቁድስ እንዲህ ይላል (ባሮቼ ሆይ  በደልን መፈፀምን በራሴ ላይ ክልክል አድርጋታለሁ በእናንተም ላይ ክልክል አድርጋታለሁ አትበደደሉ (ሙስሊም)በዳይ እና ተበዳይን እኩል ማገዝ እንዳለብን ነብዩ ሰ.ወ.ዐ በሀዲሳቸው እንዲህ ይሉናል(በዳይ ወንድምህን አግዘው ተበዳይን አግዘው አሉ አንድ ሰው ከተበደለ አግዘዋለሁ በዳይ ከሆነ ግን እንዴት ብየ አግዘዋለሁ አለ ? ከመበደል እንዲቆጠብ ትክለክለዋለህ ይህ ለሱ እርዳታ ነው(ሙስሊም)በተቃራኒው ደግሞ እስልምና ከራሰ ጋር ሆነ ከሌላው ወገን በቃልም በድርጊትም ፍፁም ፍትህዊ መሆንን ያዛል፡፡አላህ እንዲህ ይላል

إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُ بِالْعَدْلِ وَالْإِحْسَانِ وَإِيتَاءِ ذِي الْقُرْبَىٰ وَيَنْهَىٰ عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ وَالْبَغْيِ ۚ يَعِظُكُمْ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ [١٦:٩٠]

«አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፡፡ ከአስከፊም (ከማመንዘር)፣ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ ከመበደልም ይከለክላል፡፡ ትገነዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል፡፡» (አል ነሕል 90)

ፍትሕ በምቾት ጊዜም በክፍ ጊዜም ከሙስሊሙም ሙስሊም ካልሆነ ወገን አሰፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡አላህ እንዲህ ይላል

ادْفَعْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ فَإِذَا الَّذِي بَيْنَكَ وَبَيْنَهُ عَدَاوَةٌ كَأَنَّهُ وَلِيٌّ حَمِيمٌ [٤١:٣٤]

«በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ጸባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር፡፡ ያን ጊዜ ያ ባንተና በእርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይኾናል፡፡»(**ፍሲለት** 34)

**ማጠቃለያ**

በመጨረሻ ይህ መፅሀፍ ለሽብርተኝነት፡እስልምና ሀይማኖት ያለው አቋም ጠቅለል ባለ መልኩ አሳይቷል ።በትክክል ርዕሱ የያዘውን ሚሰጥራዊነት ያልገለፅኩ መሆኔን አምናለሁ።ነገር ግን ከሙስሊሙ ወጭ ያለው ማህበረሰብ ጋር የሚደረግ ግንኙነት፣ የጋራ ጥቅም፣መልካምነት እና ፍቅር ጨምሮ አጠቃላይ የሆነ ፍንጭ ሰጥቻለሁ ። ኢማን ልቡ ውስጥ የፀና ፡ ከወደደ ለአላህ ብሎ ፡ ከጠላም ለአላህ ብሎ የሚጠላ እንጂ ሰሜቱን ተገዥ ሆኖ መሆን የለበትም። አንድ ሰው ስትጠላ የምትጠላው እሱነቱን ሳይሆን ፡ ጥላቻህ አላህ የከለከለውን በመድፈሩ፡ ለአላህ ትእዛዝ ቸልተኝነቱን ነው ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

خُذِ الْعَفْوَ وَأْمُرْ بِالْعُرْفِ وَأَعْرِضْ عَنِ الْجَاهِلِينَ [٧:١٩٩]

ገርን ጠባይ ያዝ። በመልካምም እዘዝ። ባለጌዎቹንም ተዋቸው።

ምነኛ ያማረ ሀይማኖት ነው ከሰማይ በመጣው መለኮታዊ ትምህርት መሰረት ሰዎች ከሰው ልጅ አገዛዝ አውጥቶ አንድ ወደ ሆነው ፈጣሪ የሚያመጣ ፡ከክህደት ና ጨለማ ፡ ከማጋራት ወደ እስልምና ብርሃን ያመጣል ። አላህ እንዲህ ይላል ፡-

اللَّهُ وَلِيُّ الَّذِينَ آمَنُوا يُخْرِجُهُم مِّنَ الظُّلُمَاتِ إِلَى النُّورِ ۖ وَالَّذِينَ كَفَرُوا أَوْلِيَاؤُهُمُ الطَّاغُوتُ يُخْرِجُونَهُم مِّنَ النُّورِ إِلَى الظُّلُمَاتِ ۗ أُولَٰئِكَ أَصْحَابُ النَّارِ ۖ هُمْ فِيهَا خَالِدُونَ [٢:٢٥٧]

‹‹አላህ የእነዚያ ያመኑት ሰዎች ረዳት ነው። ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል። እነዚያም የካዱት ረዳቶቻቸው ጣዖታት ናቸው። ከብርሃን ወደ ጨለማዎች ያወጧቸዋል። እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው፤ እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው።››(አል በቀራህ 257)

የሀይማኖት ተከታዮች ለሁሉም መልካም እና በጎ እንዲሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ ፍትህ እንዲያሰፍኑ ፍቅር ፡ መቻቻል መተዛዘን እና ይቅር ባይነት እንዲላበሱ ፡ አላህ ከከለከለው ርቀው ራሳቸውን ፡ ገንዘባቸው፡ ንብረታቸውን ጠብቀው በሰላም እንዲኖሩ ፡ ከራስ ወዳድነት ስሜት ርቀው ለሌላው መልካም እንዲሆኑ እና በጎ እንዲዉሉ፡ ትልቁ ለትንሹ እንዲያዝን ፡ ትንሹ ለትልቁ እንዲያከብር ፡ ሀብታሙ ድሀውን እንዲያግዝ ፡ በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ዘንድ የመተዛዘን ፣ የመቻቻል፣ የመፈቃቀር ስሜት እንዲጎናፀፍ እስልምና ሀይማኖት ያስተምራል ። ይህ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ በሀዲሳቸው እንዲህ በማለት ጠቅሰውታል (የአማኞች ምሳሌ የመዋደዳቸው ልክ እንደ አንድ አካል ናቸው አንዱ የሰውነት ክፍልቢታመም የተቀረው አካል ትኩሳት እና ህመም ይሰማዋል)ይህ መፅሀፍ እውነትን ለሚፈልጉ ሁሉ ማሰረጃ እንዲሆናቸው አመኛለሁ፡ ለእነዚያ ራሳቸው ከመጪው አለም (አኼራ) ዘለአለማዊ ቅጣት የሚጠብቁና፡ እነዚያ ዘለአለማዊ የጀነት ፀጋ ፍለጋ የሚራራጡ ። ጉዳዩ በጣም አስፈሪ ነው ሁላችንም እንደምናውቀው የዚች አለም መጨረሻ ሞት ነው። ነገሮች ሁሉ የሚያበቁት እዚም ላይ ቢሆን ኖሮ ቀላል ነው። ነገር ግን ከሞት ቡሃላ ትልቅ ነገር አለ።ሙስሊሞች እንደመሆናችን መጠን ከሞት ቡሃላ መቀሰቀስ እንዳለ፣ ለስራው ስራ ምንዳ እና ቅጣት እንዳለ፣ በጀነት ወይም

በእሳት ውስጥ ዘለአለማዊ ኑሮ እንዳለ እናምናለን ፡፡የሰለመና እስልምናውን ያሳመረ ከአላህ እዝነት ጀርባ ለሰራው ጥሩ ምግባር ጀነትን ያገኛል፡፡ያጠፍው ደግሞ ጥፋቱ ከሰው ሀቅ ጋር ግንኙነት ካለው ይጠየቅበታል ፡ጥፋቱ ከአላህ ጋር የተያያዘ ከሆነ ደግሞ እንደ አላህ ፍላጎት ይሆናል፡፡ሲፈልግ ይምረዋል ሲፈለግ ይቀጠዋል ፡እስልምና ሳይቀበል በክህደት እና በማጋራት የሞተ ሰው ግን መቀመጫው እሳት ይሆናል ብለን እናሰባለን፡ ለዚህም አስተዋይ የሆነ ሰው ለራሱ ዘለአለማዊ ደስታን የምትሰጠው ጀነት በማግኘት ድል የምታጎናፅፈውን ትክክለኛው መንገድ ፡ ትክክለኛውን ሀይማኖት ሊመርጥ ይገባዋል ፡፡

ሰላት ና ሰላም ለአለማት እዝነት ለተላኩ በነብዩ መሀመድ ለይ ና በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረበቸው እና የሳቸውን መንገድ በተከተሉ ሁሉ እስከአለም ፍፃሜ ይሁን ፡፡